የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት

ደቡብ ኢትዮጵያ ነጋሪት ጋዜጣ

DEBUB ETHIOPIA NEGARIT GAZETA

OF THE SOUTH ETHIOPIA REGIONAL STATE

፪ኛ ዓመት ቁጥር...
አርባምንጭ የካቲት...ቀን ፪ሺ፲፮ዓ.ም

በደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2nd Year No
Arbaminch Febuary, 2024


**ማውጫ**

**አዋጅ ቁጥር ........./፪ሺ፲፮ ዓ.ም**

**የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት የማዕድን ሥራዎችን ለማስተዳደር የወጣ አዋጅ--- ገፅ**

***መግቢያ***

*በክልላችን ውስጥ የሚገኘውን የማዕድን ሀብት ተገቢውን ጥበቃና እንክብካቤ በማድረግ በዘላቂነት ለህዝብ ጥቅም፣ እንዲውልና ለክልሉና ለሀገር ኢኮኖሚ መዋሉ በመንግስት መረጋገጥ እንዳለበት በመታመኑ፤*

*በክልሉ የሚገኙ የማዕድናት ግብይትን ሕጋዊ ስርዓት ለማስያዝና ለመቆጣጠር የሚያስችል የማዕድን ሥራ ፈቃድ አሰጣጥ ስርዓትን፤የማዕድን ገቢ ግብር፤ሮያሊቲና ልዩ ልዩ ክፍያዎችን የሚወስን የህግ ማዕቀፍ የሚያስፈልግ ሆኖ በመገኘቱ፤*

*ህጋዊ የማዕድን ማምረትና ግብይት ሥርዓትን ዘመናዊ በማድረግ እና ሕገ-ወጥነት በመቆጣጠር ክልሉ ከዚህ ሃብት አስፈላጊውን ጥቅም እንዲያገኝ የማዕድን ሥራዎች አስተዳደርን በህግ መደንገግ አስፈላጊ በመሆኑ፤*

*የክልሉ ምክር ቤት በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ህገ-መንግስት አንቀጽ 54 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡*

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ ድንጋጌ

## 1) አጭር ርዕስ

*ይህ አዋጅ "የደቡብ ኢትዮጰያ ክልል መንግሥት የማዕድን ሥራዎችን ለማስተዳደር የወጣ አዋጅ ቁጥር…/2016" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡*

## 2) ትርጓሜ

*የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-*

1) ***"ክልል"** ማለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ነው፤*
2) ***"መንግስት"** ማለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ነው፤*
3) ***"ቢሮ"** ማለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ውሃ፣ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ ወይም ተተኪው ነው፤*
4) ***"ማዕድን"** ማለት ማናቸውም ዋጋ ያለው በጠጣር፤ በፈሳሽ ወይም በጋዝ መልክ በተፈጥሮ በመሬት ላይ ወይም ውስጥ፤ በውሃ ውስጥ ወይም ስር የሚገኝ በጂኦሎጂ ሂደት ወይም ሁኔታዎች የተፈጠረ ሲሆን ቀደም ሲል ተቆፍሮ በወጣና ተራፊ የተቆለለ ማዕድን አዘል አፈር ወይም በቀሪ የማዕድን ክምችት ውስጥ የሚገኝ ማዕድንን ይጨምራል፤ ሆኖም የሚከተሉትን አይጨምርም፡-*
5) ***"ስትራተጂክ ማዕድን"** ማለት የፌዴራል ፈቃድ ሰጪ አካል ወይም ቢሮው በመመሪያ ስትራተጂክ ማዕድን ብሎ የሚሰይመው ማንኛውም ማዕድን ነው፤*
6) ***"የኮንስትራክሽን ማዕድን"** ማለት ማናቸውም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለኮንስትራክሽን በግብዓትነት የሚያገለግል እንደ ዕብነበረድ፤ ግራናይት፤ ላይምስቶን፣ባዛልት፤ አሸዋ፣ጠጠር ኢግኒምብራይትና የሸክላ አፈር የመሰለ ማዕድን ሲሆን ቢሮው በመመሪያ የኮንስትራክሽን ማዕድን ብሎ የሚሰይመውን ብረት ነክ ያልሆነ ሌላ ማዕድንን ይጨምራል፤*
7) ***"የኢንዱስትሪ ማዕድን"** ማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለኢንዱስትሪ በግብዓትነት የሚያገለግል እንደ ካኦሊን፣ቤንቶናይት፣ኳርትዝ፣የድንጋይ ከሰል፤ ላይምስቶን፤ ጂፕሰም፤ ፑሚስ፣የሸክላ አፈርና ግራፋይት የመሰለ ማንኛውም ማዕድን ሲሆን፣ብረት ነክና የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናትን ሳይጨምር ቢሮው በመመሪያ የኢንዱስትሪ ማዕድን ብሎ የሚሰይመውን ማንኛውንም ሌላ ማዕድን ይጨምራል፤*
8) ***"ብረት ነክ ማዕድን"** ማለት እንደ ብረት፤ መዳብ፤ ነሐስ፤ እርሳስ፤ ክሮማይት፤ ኒኬል፤ ታንታለም ማንጋኒስ የመሰለ ማዕድን ሲሆን፤ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናትን ሳይጨምር ቢሮው በመመሪያ ብረት ነክ ማዕድን ብሎ የሚሰይመውን ማንኛውንም ሌላ ማዕድን ይጨምራል፤*

9) **"የከበረ ማዕድን"** ማለት እንደ ፕላቲኒየም፣ወርቅና ብር የመሰለ የከበረ ብረት ነክ ማዕድን ወይም እንደ አልማዝ፣ሩቢ ኤመራልድና ሳፋየር ያለ የከበረ ድንጋይ ሲሆን፣ ቢሮው በመመሪያ የከበረ ማዕድን ብሎ የሚሰይመውን ማናቸውንም ሌላ ማዕድን ይጨምራል፣

10)**"በከፊል የከበረ ማዕድን"** ማለት ለማስዋቢያነት የሚውል ወጥ ወይም በተፈጥሮአዊ አንድነት የተጣመረ እንደ ኦፓል፣ ሮዶላይት፣ ኦሊቪን፣ጃዳይትና ላዙራይት የመሰለ ማዕድን ሲሆን፣ የከበሩ ማዕድናትን ሳይጨምር ቢሮው በመመሪያ በከፊል የከበረ ማዕድን ብሎ የሚሰይመውን ማንኛውንም ሌላ ማዕድን ይጨምራል፣

11) **"ባህላዊ የማዕድን ማምረት ሥራ"** ማለት አብዛኛው ተግባር በእጅ የሚከናወን እና ተቀጣሪ ሠራተኛ የማይሳተፍበት በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ወይም በሥራ ዕድል ፈጠራ ወይም ሌሎች ህጋዊ አደረጃጀቶችን ተከትለው በተደራጁ ሥራ ፈላጊ ወጣቶች የሚከናወን የማዕድን ማምረት ሥራ ነው፣

12) **"ልዩ የአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ"** ማለት የባህላዊ ማዕድን ማምረት ስራ ፈቃድ ተሰጥቶአቸው ማዕድን እያመረቱ ያሉና የገንዘብ አቅማቸው ዘመናዊ የማምረቻ መሳሪያዎችን በመጠቀም ማምረት በሚያሥችላቸው ማህበራት የሚከናወን የማእድን ማምረት ሥራ ነው፣

13) **"አነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ"** ማለት ከማዕድኑ ሥፍራ በአመት የሚመረተው የማዕድን አዘል አፈርና ድንጋይ መጠኑ ከሚከተለው የማይበልጥ ማዕድን የማምረት ሥራ ነው፣

ሀ) እንደ ካኦሊን፣ቤንቶናይት፣ ዲቶማይት፣ዶሎማይት ኳርትዝና የድንጋይ ከሰል የመሳሰሉት የኢንዱስትሪ ማዕድናትን በሚመለከት 120,000 ቶን፣

ለ) የኮንስትራክሽን ማዕድናትን በሚመለከት፡-

1) አሸዋ፣ ጠጠር፣ ፑሚስ፣ኢግኒምብራይት፣ የሸክላ አፈርና የመሳሰሉትን በሚመለከት 80,000ሜትር ኩብ፣

2) እብነበረድ፣ግራናይትና የመሳሰሉትን የዳይሜኒሽን ድንጋዮች በሚመለከት 10,000ሜትር ኩብ፣

ሐ) የጂኦተርማል ክምችትን በሚመለከት፡-

1) ለመታጠቢያ፣ ለመዝናኛና ለሕክምና አገልግሎት የሚውሉትን በሚመለከት 2,000,000ሜትር ኩብ፣

2) ከድንጋይ ወይም ከብራይን የሚመረቱ የጨው ዓይነቶችን በሚመለከት 14,000 ቶን፣

14) **"ከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ"** ማለት ከማዕድኑ ሥፍራ በአመት የሚመረተው የማዕድን አዘል አፈርና ድንጋይ መጠን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(13)ከተመለከተው መጠን በላይ የሆነ ማዕድናትን የማምረት ሥራ ነው፣

15) **"የማዕድን ሥራ"** ማለት ከማዕድን ምርመራ፣ይዞ መቆየት ወይም ማምረት ጋር የተያያዘ ተግባር ነው፣

16) **"ይዞ መቆየት"** ማለት የማዕድን ምርመራ ሥራ ፈቃድ በተሰጠበት ቦታ ላይ ለማዕድን ምርመራ ሥራ የተሰጠው የጊዜ ገደብ ተጠናቆ ማዕድን ወደ ማምረት ደረጃ መሸጋር የማይቻል ሆኖ ከተገኘ የምርመራውን ፈቃድ መብት ለተወሰነ ጊዜ ይዞ መቆየት ማለት ነው።

17) **"ምርመራ"** ማለት ሆን ብሎ ማዕድን ለማግኘት በማናቸውም የገጸምድር ወይም ከርሰምድር፣ በውሃ አካላት እንዲሁም ቀደም ሲል ተቆፍሮ በወጣና በቀረ የተቆለለ ማዕድን አዘል አፈር ወይም አለት ውስጥ በአካባቢ ላይ ለውጥ በማያስከትል መልኩ በፎቶግራፍና ምስሎች፣ በጂኦሎጂ፣ በጂኦፊዚክስ፣ በጂኦኬሚስትሪ፣ በተለያዩ የጉድጓድ ቁፋሮና በመሳሰሉት ዘዴዎች አማካኝነት የማዕድኑን መኖር፣ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታውን እና መጠኑን ለማወቅና ለማጣራት የሚደረግ ሥራ ነው፣

18) **"ማዕድን ማምረት"** ማለት በማናቸውም አይነት ዘዴ በሚከናወን ሥራ ማዕድንን በገጸምድር፣ በከርሰምድር ወይም በውሃ አካላት ከሚገኝ የማዕድን ክምችት ወይም ተራፊ የማዕድን ክምችት ውስጥ ለማውጣት የሚደረግ ሥራ ሲሆን ከዚህ ጋር የተያያዘ ማከማቸትን፣ማዘጋጀትን፣ፕሮሰስ ማድረግን(ማቅለጥንና ማጣራትን ሳይጨምር)፣ ማጓጓዝንና መሸጥን ይጨምራል፣

ሀ) ለመታጠቢያ፣ለመዝናኛ፣ ለሕክምና ከሚውል የጂኦተርማል ውሃ እና ከውስጡ ማዕድን ለማውጣት ከሚውል እንደ ብራይን ውሃ በስተቀር ሌላውን ውሃ፣

ለ) አግባብ ባለው የነዳጅ ሕግ ትርጓሜ የሚካተቱ የተፈጥሮ ዘይትና ጋዝን፣

ሐ) ለም አፈርን (ላይኛው አፈር) እና ነዳጅ አዘል አለትን (ነዳጅ አዘል ሼል)

19) **"ፈቃድ"** ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጥ የማዕድን ምርመራ፣ይዞ የመቆየት ወይም ማምረት ፈቃድ ነው፣

20) **"የፈቃድ ክልል"** ማለት ማናቸውም ፈቃድ የተሰጠበት ስፍራ ነው፣

21) **"ባለፈቃድ"** ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ የምርመራ፣ይዞ የመቆየት ወይም የማምረት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም ተተኪው ነው ነው፣

22) **"የማምረት ፈቃድ"** ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጥ የከፍተኛ ደረጃ፣የአነስተኛ ደረጃ፣ የልዩ አነስተኛ ደረጃ ወይም የባህላዊ ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ነው፣

23) **"የማዕድን መብት"** ማለት ከምርመራ፣ይዞ ከመቆየት ወይም ከማምረት ፈቃድ ጋር የተያያዘ መብት ነው፣

24) **"ተራፊ ማዕድን አዘል ቁልል"** ማለት ከማዕድን ሥራ የተገኘ ወይም በማዕድን ሥራው ምክንያት የወጣና በማዕድን ባለፈቃዱ እንደገና ጥቅም ላይ ለማዋል ታስቦ ተቆልሎ፣ ተቀምጦ ወይም ተጠራቅሞ የነበረ ወይም የተተወ ማናቸውም ፍራሽ፣ውዳቂ፣አሰር፣ዝቃጭ፣ብጣሪ፣ቆሻሻ አዘል ድፍርስ፣ውዳቂ ድንጋይ፣ከብረት ማቅለጫ የሚወጣ አሸዋ፣ የማበልጸጊያ ፋብሪካ ቆሻሻ፣ አመድ ወይም ማናቸውም ተረፈ ምርት ነው፣

25) **"ተራፊ ክምችት"** ማለት የማዕድን ፈቃድ ሲቋረጥ፣ሲሰረዝ ወይም ዘመኑ ሲያበቃ የነበረ ማናቸውም ተራፊ ማዕድን አዘል ቁልል ነው፣

26) ***"የማዕድን ማምረት ቅድመ ዝግጅት"*** *ማለት ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣንና ባለፈቃዱ የማዕድን ማምረት ውል ከተፈራረሙበት ቀን ጀምሮ የምርት ሥራው እስከሚጀመርበት ጊዜ ድረስ እንደ ማዕድኑ ዓይነትና ጸባይ ማዕድኑን ለማምረት አስፈላጊ የሆኑ ወደ ማዕድን ክምችቱ ለመድረስ ማዕድን አዘሉን አካል ለማውጣት፤ ለመፍጨት፤ለማበልጸግ፤ማዕድኑን ለማምረት እና ለማዕድን ማምረት ሥራው አገልግሎት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ግንባታዎች የሚከናወኑበት የዝግጅት ጊዜ ነው፤*

27) ***"የሥራ ፕሮግራም"*** *ማለት እንደነገሩ አግባብነት ለምርመራ ወይም ለማምረት ሥራ የሚቀርብ ዝርዝር ስራውን፤ሥራው የሚከናወንበትን ጊዜ፤ ወጪውን፤ መዋቅሩንና የሰው ሃይል ስብጥሩን የሚያመላክት ዕቅድ ነው፤*

28) **"የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት"** ማለት በማዕድናት ግብይት ሥራ ላይ ለመሳተፍ የሚያስችል የንግድ ፈቃድ ለማግኘት ብቁ ስለመሆኑ የሚሰጥ ሠነድ ነው፡፡

29)**"አቅራቢነት"** ማለት በክልሉ ውስጥ የተመረቱ ወርቅና ብር ማዕድናትን ከሕጋዊ አምራች በመግዛት ለብሔራዊ ባንክ አካል፤ ከወርቅና ብር ውጪ ያሉ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናትን ለላኪዎች ወይም የመቅረጽ የዕደ ጥበብ ፈቃድ ላላቸው እና ከእነዚህ ውጪ ያሉትን ማዕድናት ለተጠቃሚዎች የመሸጥ ሥራ ነው፡፡

30) **"ዕደ-ጥበብ"** ማለት ከከበሩ ወይም በከፊል ከከበሩ ወይም ከብረት ነክ ማዕድናት በማንጠር ወይም በመቅረጽ ወይም የሁለቱን ውጤት አጣምሮ ሌላ ቅርጽ በማስያዝ ማዕድናት የመጨረሻ ቅርጻቸውን እንዲይዙ የማድረግ ሥራ ነው፡፡

31) **"ማንጠር"** ማለት የከበሩ ብረት ነክ ማዕድናትን ለተጠቃሚ ፍጆታ በሚሆን መልኩ ማቅለጥ፤ ቅርጽ ማውጣትና ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን ማከናወን ነው፡፡

32) **"መቅረጽ"** ማለት የከበሩና በከፊል የከበሩ የጌጣጌጥ ማዕድናትን የመጨረሻቸውን ቅርጽ እንዲይዙ ለማድረግ የሚከናወን የመቁረጥ፤ቅርጽ የማውጣት፤የማለስለስና ሌሎች ተመሳሳይ ሥራዎችን ማከናወን ነው፡፡

33) **"ማጣመር"** ማለት በማንጠር ወይም በመቅረጽ ሥራ የተሰራ ያለቀለት ወይም በከፊል ያለቀለት ጌጥ የማምረት ሥራ ነው፡፡

34) ***"ነጻ ተጠቃሚ"*** *ማለት የኮንስትራክሽን ማዕድናትን ለንግድ ላልሆነ አላማ ሆኖ ለቤት ግንባታ፣ ለመንግስት መሰረተ ልማት ግንባታ ሌሎች ተመሳሳይ ለህዝብ አገልግሎት ሊውሉ የሚችሉ ተቋማትን ለመገንባት ፈቃድ ሰጪ መስሪያ ቤትን በቅድሚያ በማስፈቀድ ያለ ክፍያ አምርቶ የሚጠቀም አካል ነው፡፡*

35) ***"መደበኛ ያልሆነ የማዕድን አምራች"*** *ማለት ለአካባቢው የግንባታ ግብዓት ፈላጊ የኮንስትራክሽን ማዕድናትን በበቂ መጠን ማቅረብ የሚችል ህጋዊ የማዕድን ማምረት ስራ ባለፈቃድ በማይኖርበት አካባቢ እንደ አስፈላጊነቱ የሥራ ዕቅድ በማቅረብና ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣንን*

*በቅድሚያ በማስፈቀድ የኮንስትራክሽን ማዕድናትን በውል ለያዘው የግንባታ ሥራ በጊዜያዊነት አምርቶ በክፍያ የሚጠቀም አካል ነው፤*

36) ***"የማዕድን ቁርጥ ዋጋ ተመን"*** *ማለት የማምረቻ ወጪን ሳይጨምር ማዕድን በሚመረትበት አካባቢ ያለውን የገበያ ፍላጎትና የአቅርቦት ሁኔታ መሰረት በማድረግ የተተመነ የማዕድናት የሽያጭ ዋጋ ነው፤*

37) ***"ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን"*** *ማለት እንደአግባቡ የክልሉ ውሃ፤ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ ወይም ማዕድን ዘርፍን በሚመለከት ኃላፊነት የተሰጠው የዞን፤የወረዳ እና የከተማ አስተዳደር አካል ነው፤*

38) ***"ሮያሊቲ"*** *ማለት የማዕድን ሀብት ባለቤት ለሆነው መንግስትና ሕዝብ ባለፈቃድ ከማዕድን ማምረቻ ቦታ ላይ ከሚያመርተው የማዕድን/ናት/ምርት በየጊዜው በመቶኛ እየተሰላ የማምረቻና ሪስክ ወጪን ሳይጨምር የሚከፍለው ክፊያ ነው፤*

39) ***"የማዕድን ሥራ ገቢ ግብር"*** *ማለት በክልሉ ዉስጥ ከሚካሄዱ የማዕድን ማምረት ሥራዎች በሂሳብ ዓመቱ በተገኘ ማናቸዉም ገቢ ላይ የተፈቀዱ የሥራ ማስኬጃ ወጪዎችን፣የካፒታልና የቅድመ-ምርት ወጪዎችን፣የሪኢንቨስትመንት ቅናሽንና የተፈቀዱ ኪሣራዎችን በመቀነስ የሚሰላ የመንግስት ግብር ነዉ፤*

40) **"ተቆጣጣሪ"** ማለት የማዕድን ሥራ እንዲቆጣጠር ሥልጣን ባለው የመንግሥት ተቋም ኃላፊነት የተሰጠው ሰው ነው፤

41) ***"ውል"*** ማለት ማዕድን ለመመርመር፣ ይዞ ለመቆየትና ለማምረት በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣንና በባለፈቃዱ መካከል የሚደረግ ውል ማለት ነው፡፡

42) ***"የአገር ውስጥ ባለሀብት"*** *ማለት የኢንቨስትመንት ካፒታል በሥራ ላይ ያዋለ ኢትዮጵያዊ ወይም መንግስትንና የመንግስት የልማት ድርጅትን እንዲሁም እንደ አገር ውስጥ ባለሀብት መቆጠር የፈለገ በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆነ የውጭ አገር ዜጋን ይጨምራል፤*

43) ***"ማስተላለፍ"*** *ማለት መሸጥ፤በዕዳ ማስያዝ፤ማውረስ፤መዳረግ ወይም በሌላ መንገድ ማስተላለፍ ነው፤*

44) ***"መዝገብ"*** *ማለት በዚህ አዋጅ የተመለከተው የማዕድን መብቶች የተመዘገቡበት መዝገብ ወይም የኤሌክትሮኒክስ የማዕድን ካዳስተር ነው፤*

45) ***"ፈቃድ ተፈጻሚ የሆነበት ቀን"*** *ማለት የማዕድን ማምረት ፈቃድ ጠያቂው እና ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የማዕድን ማምረት ስምምነት የተፈራረሙበት ቀን ሲሆን ለሌሎች የማዕድን ሥራዎች ፈቃድ መሰጠቱን የሚገልጽ ደብዳቤ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የተፈረመበት ቀን ነው፤*

46) ***"ቀን"*** *ማለት በቀን መቁጠሪያ ላይ የሰፈረ ማንኛውም ቀን ሲሆን፤ በዚህ አዋጅ፤በደንብ ወይም በመመሪያ የተመለከተ ተግባርን ለማከናወን የተወሰኑ ቀናት ተቆርጠው ከሆነ ቀናቱ የሚወሰኑት*

*የመጀመሪያውን ቀን በመቀነስ እና እሁድና ቅዳሜ ወይም በሕዝብ በአላት ላይ እስካልዋለ ድረስ የመጨረሻውን ቀን በመጨመር ይሆናል፤*

*47) **"ማህበር"** ማለት በማዕድን ማምረት ስራ ላይ ለመሰማራት ፣ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ወይም በሥራ ዕድል ፈጠራ ወይም ሌሎች ህጋዊ አደረጃጀቶችን ተከትለው የተደራጁ አባላትን ያቀፈ ስብስብ ነው፤*

*48) **"ሰው"** ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤*

*49) ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡*

### 3) የተፈጻሚነት ወሰን

*ይህ አዋጅ በክልሉ ውስጥ በሚካሄዱ የማዕድን ሥራዎችና ተዛማጅ ተግባራት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡*

## ***ክፍል ሁለት***

## ***የማዕድን ሀብት ልማት ሥራ መሰረታዊ ዓላማና መርሆዎች***

### *4) ዓላማ*

*የዚህ አዋጅ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-*

*1) መንግስት የክልሉን የማዕድን ሀብት የማስተዳደር እና የመጠበቅ ስልጣንና ኃላፊነት ተግባራዊ ለማድረግ፤*

*2) የክልሉን ኢኮኖሚዊና ማህበራዊ ዕድገት እንዲያፋጥንና የስራ እድል በስፋት እንዲፈጠር ለማድረግ፤*

*3) በክልሉ ውስጥ የማዕድን ልማት ሥራ ላይ ለተሰማሩ ባለሃብቶች የህግ ከለላ ለመስጠት፤*

*4) የክልሉን የማዕድን ሃብት ሥርዓትና ዘላቂነት ባለው ሁኔታ መልማቱን ማረጋገጥ*

### *5) መሬትን ከልሎ ስለመጠበቅ*

*1) በክልሉ ውስጥ የሚገኝና የማዕድን ሀብት ያለው መሬት ለማዕድን ልማት ሥራ ይውላል፡፡*

*2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ መንግሥት ለህዝብ ጥቅም አስፈላጊ ነው ብሎ ባመነበት ጊዜ ለህዝብ ማስታወቂያ በማውጣት በማንኛውም መሬት ላይ የማዕድን ሥራ እንዳይካሄድ ሊከለክል ይችላል፡፡*

*3) ማንኛውም ሰው ቀጥሎ በተዘረዘሩት ሥፍራዎች ላይ የማዕድን ምርመራ ፈቃድ፤ ይዞ የመቆየት ፈቃድ ወይም የማምረት ፈቃድ አይሰጠውም፡፡*

*ሀ) ታሪካዊ ሥፍራዎች፤ ለባህላዊ ኩነቶች፤ ለመቃብር፤እምነት የሚካሄድበት እና በህግ ሥልጣን ባለው አካል የተመዘገበ ሌላ የማህበራዊ አገልግሎት ሥፍራ፤*

*ለ) ለተፈጥሮ አካባቢ ጥበቃ ወይም ለፓርክ በተከለሉ ሥፍራዎች፤*

*ሐ) ለጉዳዩ ስልጣን የተሰጠው አካል ካልፈቀደ በቀር ከመንደሮች፤ከከተማዎች ወይም ከውሃ ማጠራቀሚያዎች ወይም ከግድቦች በ500ሜትር ክልል ውስጥ፤ ወይም፤*

*መ) በሌላ ሕግ በተከለከሉ ቦታዎች፡፡*

*4) መንግስት ለብሔራዊ ጥቅም ሲባል ተገቢው የማካካሻ እርምጃ ተወስዶ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ወይም (3) መሠረት የተከለለ ማንኛውም ሥፍራ ለማዕድን ሥራ ክፍት እንዲሆን ሊፈቅድ ይችላል፡፡*

## *6) የፈቃድ አስፈላጊነት*

*1) ማንኛውም ሰው ህጋዊ የሆነ የማዕድን ሥራ ፈቃድ ሳይኖረው የማዕድን ሥራዎችን ማካሄድ፤ በተፈጥሮአዊ ሁኔታ ማዕድን መያዝ ማዘዋወር ወይም መሸጥ አይችልም፡፡*
*2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው ቢኖርም፣ ሕጋዊ የመሬት ባለይዞታ የሆነ ሰው የኮንስራክሽን ማዕድናትን በይዞታው ስር ከሚገኝ መሬት ላይ ፍቃድ ሳያስፈልገው ለንግድ ላልሆነ ዓላማ አምርቶ በግሉ መጠቀም ይችላል፡፡*
*3) የመሠረተ ልማት አውታሮችን የሚሰራ ማንኛውም ሰው ፈቃድ ሰጪውን አካል አስቀድሞ በማስፈቀድ በመንግስት የሚካሄዱ ፕሮጀክቶች ወይም በግንባታ ውል ውስጥ የማዕድኑ ዋጋ ያልተካተተ ከሆነ የኮንስራክሽን ማዕድናትን ያለ ክፍያ በነጻ አምርቶ መጠቀም ይችላል፡፡*
*4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ከሥራው የሚቀረው የተመረተው ማዕድን ለመንግስት ገቢ መደረግ አለበት፡፡ ገቢ የሚሆንበት ሁኔታ በሚወጣው ደንብ የሚወሰን ይሆናል፡፡*

## *7) በመንግስት ስለሚካሄዱ የማዕድን ሥራዎች*

*መንግስት ለጠቅላላ የኢኮኖሚ ዕድገት ወሳኝ የሆኑ የማዕድን ሥራዎችን በራሱ ወይም ከግል ባለሀብቶች ጋር በቅንጅት ሊሰራ ይችላል፡፡*

## *8) መደበኛ ያልሆነ የማዕድን ሥራና የማዕድን ቁርጥ ዋጋ*

*1) በተወሰነ ጊዜ ገደብ ውስጥ የሚጠናቀቁ የህንጻ፣ የመንገድና ሌሎች የመሰረተ ልማት ግንባታ ስራ ላይ የተሰማሩ ተቋራጮች የግንባታ ማዕድናት በሚፈልጉት ጊዜና መጠን በአካባቢው ከሚገኙ ህጋዊ አምራቾች ማግኘት የማይችሉበት ሁኔታ ሲያጋጥም እንደ አስፈላጊነቱ የሥራ ዕቅድ በማቅረብና ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣንን በቅድሚያ በማስፈቀድ የኮንስትራክሽን ማዕድናትን በውል ለያዙት የግንባታ ሥራ በጊዜያዊነት አምርቶ በክፍያ መጠቀም ይችላሉ፡፡ የፈቃድ አሰጣጡና ክፍያዎችን በተመለከተ በሚወጣው ደንብና መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡*

*2) የግንባታ ማዕድናትን በማምረት ለግንባታዉ ኢንዱስትሪ በግብዓትነት መጠቀም የሚፈልጉ ወይም ከማንኛዉም ህጋዊ ሶሾ-ኢኮኖሚክ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ መልኩ የተመረቱ የግንባታ ማዕድናትን መሸጥ የሚፈልጉ አካላትን የሚያስተናግድ የግንባታ ማዕድናት ቁርጥ ዋጋ ክፍያ ተመን ተጠንቶ ቢሮዉ በሚያወጣዉ መመሪያ ይወሰናል፡፡*

# ክፍል ሶስት

# ስለፈቃድና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሥርዓት

## ንዑስ ክፍል አንድ

## ስለ ማዕድን ሥራዎች ፈቃድ አሰጣጥ እና አፈጻጸም ሥርዓት

### 9) የፈቃድ ዓይነቶች

በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ፈቃዶች ሊሰጡ ይችላሉ፡-

1) የምርመራ ፈቃድ
2) ይዞ የመቆየት ፈቃድ
3) ባህላዊ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ (ከብረትና ብረት ነክ ማዕድናት ውጪ)
4) ልዩ-አነስተኛ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ (ከብረትና ብረት ነክ ማዕድናት ውጪ)
5) የአነስተኛ ደረጃ የኮንስትራክሽንና የኢንዱስትሪ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ
6) የከፍተኛ ደረጃ የኮንስትራክሽን ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ

### 10) የማዕድን ፈቃድ ስለመስጠት

1) በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ደረጃ አግባብ ባለው ሕግ መሰረት የሚሰጠው የማዕድን ፈቃድ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በክልሉ ውስጥ የማዕድን ፈቃድ የሚሰጠው፣የሚታደሰው፣ የሚሰረዘው ወይም የሚቋረጠው በክልሉ ፈቃድ ሰጪ ይሆናል፤

2) ከፈቃድ ሰጪው ኣካል ውጪ በማንኛውም አካል የማዕድን ፈቃድ መስጠት፣ ማደስ፣ መሰረዝ ወይም ማቋረጥ የተከለከለ ነው፡፡

### 11) ፈቃድ ለማግኘት ብቁ ስለመሆን

1) የማዕድን ሥራዎች ፈቃድ ለማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡-

(ሀ) በንግድ ሕግ መሰረት የንግድ ሥራን ለማከናወን የሚችል ሰው፤

(ለ) በህግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የተሰጠ የአካባቢና የህብረተሰብ ተፅዕኖ ጥናት ማስረጃ ማቅረብ፤
(ሐ) ለስራው የሚያስፈልገውን የገንዘብ፣ የቴክኒክና የሙያ ችሎታ መኖር፤

(መ) ኪሳራ ውስጥ የሌለ ወይም ከአበዳሪዎች ጋር በገባው የብድር ውል መሰረት ከፍሎ የጨረሰ ሰው ከሆነ፤

(ሠ) በመፍረስ ላይ የሌለ የንግድ ድርጅት፤ እና

(ረ) በሀሰተኛ ማስረጃ ወይም በማታለል ተግባር ፈቃዱ ያልተሰረዘበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 1(ሀ-ሠ) ሥር የተደነገገው መስፈርት በባህላዊ የማዕድን ማምረት ፈቃድ ጠያቂዎች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

*3) በማጭበርበር ወይም የተሳሳተ መረጃ በማቅረብ ፈቃዱ የተሰረዘበት ባለፈቃድ ፈቃዱ ከተሰረዘበት ቀን አንስቶ ለአምስት አመታት ሌላ ፈቃድ ማግኘት አይችልም፡፡*

## *12) ስለፈቃድ ማመልከቻ*

*1) የማዕድን ፈቃድ ለማግኘት፣ ለማደስ ወይም ለማስተላለፍ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ማመልከቻውን ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በሚያዘጋጀው ቅፅ ላይ በመሙላት ለባሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡ ዝርዝሩ በሚወጣው ደንብ የሚወሰን ይሆናል፡፡*
*2) ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን የቀረበውን ማመልከቻ በማጤን በዚህ አዋጅ ሥር የተደነገጉትን አስፈላጊ መስፈርቶች መሟላታቸው ካረጋገጠ መዝግቦ ለአመልካቹ ፍቃዱን ይሰጣል፡፡*

## *13) ማመልከቻዎች ስለሚስተናገዱበት ቅደም ተከተል*

*1) ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የማዕድን ፍቃድ በሚሰጥበት ጊዜ በሥራ ዕድል ፈጠራ ወይም በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ወይም በሌሎች አደራጅ መ/ቤቶች ለተደራጁ ሥራ-ፈላጊ ማህበራት ለማበረታት ወይም ማዕድኑ ለኢኮኖሚያዊ ዕድገት መዋል ይችላል ብሎ በሌላ አኳኋን ካልወሰነ በቀር፡-*

*ሀ) ለከፍተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ፈቃድ የቀረበ ማመልከቻ ለአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት፤ልዩ አነስተኛና ለባህላዊ የማዕድን ማምረት ፈቃድ በቀረቡ ማመልከቻዎች እንዲሁም ለአነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ፈቃድ የቀረበ ማመልከቻ ልዩ አነስተኛና ለባህላዊ የማዕድን ማምረት ፈቃድ በቀረበ ማመልከቻ ላይ ቀዳሚነት ይኖራቸዋል፤*

*ለ) ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ለአንድ ዓይነት ማዕድን በአንድ ቦታ ላይ አንድ ዓይነት ደረጃ ላላቸው ፈቃዶች ከአንድ በላይ ማመልከቻዎች ከቀረቡለት ማመልከቻዎቹ በቀረቡበት ቅደም ተከተል መሰረት ማስተናገድ አለበት፤*

*ሐ) ሁለት ወይም ከዚያ በላይ አመልካቾች ለአንድ ዓይነት ማዕድን በአንድ ቦታ ላይ በአንድ ጊዜ አንድ ዓይነት ደረጃ ላላቸው ፈቃዶች ማመልከቻዎቻቸውን አቅርበው ከሆነ ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ቅድሚያውን ለመወሰን ማመለክቻዎቹን የሚገመግም የቴክኒክ ቡድን ያቋቁማል፤ የቴክኒክ ቡድኑ አመልካቾቹ ያቀረቡትን የቴክኒክ ሥራ ዕቅድ፤ለሥራው ሊያወጡ ያሰቡትን የገንዘብ መጠን እና የአመልካቾቹን ብቃት ገምግሞ በውጤቱ መሠረት ቀዳሚውን ይወስናል፡፡*

*2) ሁለት ወይም ከዚያ በላይ አመልካቾች በአንድ ቦታ ላይ የፈቃድ ማመልከቻዎቻቸውን በአንድ ጊዜ ለፌዴራል ማዕድን ሚኒስቴር እና ለክልል ፈቃድ ሰጪ ባለስልጣን አቅርበው ከሆነ ሚኒስቴሩና የክልል ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ማመልከቻዎቹን የሚገመግም የጋራ የቴክኒክ ቡድን ያቋቁማሉ፤የቴክኒክ ቡድኑ አመልካቾቹ ያቀረቡትን የቴክኒክ ሥራ ዕቅድ፤ ለሥራው ሊያወጡ ያሰቡትን የገንዘብ መጠንና የአመልካቾቹን ብቃት ገምግሞ በውጤቱ መሰረት ቀዳሚውን ይወስናል፡፡*

*3) ሴት አመልካች ካለችና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) መሠረት የተካሄደው የግምገማ ውጤት እኩል ከሆነ ቅድሚያ ይኖራታል፡፡*

*4) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፤ (2) እና (3) ድንጋጌዎች ቢኖሩም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ማመልከቻ የቀረበበትን ሥፍራ ጨረታ ሊያወጣበት ይችላል፡፡*

## *14) ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ሰዎች ስለማሳወቅ*

1) ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን በዚህ አዋጅ መሰረት የቀረቡትን ማመልከቻ ከመዘገበ በኋላ፣ ጥያቄው የቀረበበትን ቦታ ወሰን፣ ስፋት እና የሚገኝበትን አድራሻ በመጥቀስ በየደረጃው የሚገኙ የሚመለከታቸው የዞን፤የወረዳ እና የቀበሌ አካላት ቦታው ለማዕድን ሥራ የተከለከለ ያለመሆኑን እንዲያረጋግጡና የፈቃድ ጥያቄውንም አስመልክቶ አስተያየት ጭምር እንዲሰጡ ይደርጋል።

2) ፈቃድ የተጠየቀበትን ቦታ አስመልክቶ ተቃውሞ ወይም ስምምነት ካለ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በደብዳቤ ከተጠየቀበት ቀን ጀምሮ በ15 (አስራ አምስት) የስራ ቀናት ውስጥ ከነምክንያቱ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማሳወቅ ይኖርባቸዋል።

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር በተደነገገው መሰረት ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የቀረበውን ተቃውሞ ከተቀበለ ለአመልካቹ ከነምክንያቱ በጽሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል።

## 15) የምርመራ ፈቃድ ስለመስጠት

1) የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሚከተሉት ሁኔታዎች ከተሟሉ የብቻ የሆነ መብት የሚያስገኝ የማዕድን ምርመራ ፈቃድ ይሰጣል።

ሀ) አመልካቹ ከዚህ በፊት በተመሳሳይ ወይም በሌሎች የልማት ዘርፎች ላይ ኢንቨስትመንት ካፒታሉን ሥራ ላያ ያወለ ከሆነና የታሰበውን የማዕድን ምርመራ ሥራ በቀረበው የሥራ ፕሮግራም መሰረት ለማከናወን የሚያስችል የገንዘብ አቅምና አስፈላጊው የቴክኒክ ችሎታ ያለው መሆኑን ካረጋገጠ፤

ለ) የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማው ተቀባይነት ካገኘ፤

ሐ) የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የምርመራ ፈቃድ ለአመልካቹ የማይሰጠው ከሆነ ይህንኑ ውሳኔ በጹሑፍ ከነምክንያቱ ለአመልካቹ ያሳውቀዋል።

## 16) የማዕድን ምርመራ ፈቃድ ጸንቶ ስለሚቆይበት ጊዜና እድሳት

1) የማዕድን ምርመራ ፈቃድ በፈቃዱ ላይ ለተገለጸው ጊዜ ጸንቶ ይቆያል፤ ሆኖም ይህ ጊዜ ከ1ዓመት በላይ ሊሆን አይችልም።

2) የምርመራ ፈቃድ በፈቃዱ ላይ በመጀመሪያ ከተገለጸው ጊዜ ለማይበልጥ ጊዜ ለሁለት ጊዜ ሊታደስ ይችላል። ባለፈቃዱ ቀደም ሲል ካቀረበው የሥራ ፕሮግራም ተጨማሪ የምርመራ ተግባር ማከናወን እንደሚያሥፈልግ ካረጋገጠና በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ተቀባይነት ካገኘ የምርመራ ፈቃዱ ሊታደስ ይችላል።

## 17) ስለማዕድን ምርመራ ባለፈቃድ መብትና ግዴታዎች

1) አግባብ ያላቸው የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፤ የማዕድን ምርመራ ባለፈቃድ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፦

ሀ) ይዞ የመቆየት ፈቃድ እንዲሰጠው የማመልከትና የማግኘት መብት

ለ) በማዕድኑና ከምርመራ ፈቃዱ ክልል ጋር በተያያዘ የማምረት ፈቃድ ለማግኘት የማመልከትና ፈቃድ የማግኘት መብት፤

ሐ) በቅድሚያ ከፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የጽሑፍ ስምምነት በማግኘት ምርመራ፤ሙከራና ትንተና ለማድረግ አስፈላጊ በሆነው መጠን ማንኛውንም የማዕድን ናሙና ለማውጣትና ለማጓጓዝ፤ ሆኖም ማዕድናቱ የመንግስት ንብረት ሆነው ይቆያሉ፤ ያለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ፈቃድ አይሸጡም።

2) አግባብ ያላቸው የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፤ የማዕድን ምርመራ ባለፈቃድ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፦

ሀ) የማዕድን ምርመራ ተፈጻሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ከ30-45 ቀናት ውስጥ የምርመራ ሥራውን የመጀመር፤

ለ) የምርመራ ፈቃዱን ስምምነቶችና ግዴታዎች የማክበር፤

ሐ) ምርመራ፤ሙከራና ትንተና ለማድረግ ያወጣቸውና ያንኳዛቸው ማዕድናትን ናሙና ቅጂዎች የማስቀመጥ፡፡

## 18) የሥራ ፕሮግራም ስለመለወጥ

1) የምርመራ ባለፈቃድ ተቀባይነት አግኝቶ የነበረውን የሥራ ፕሮግራም በማናቸውም ጊዜ ለመለወጥ ማመልከት ይችላል፡፡

2) ማንኛውም የሥራ ፕሮግራም ለውጥ ለማድረግ የሚቀርብ ማመልከቻ፡-

ሀ) ተቀባይነት አግኝቶ የነበረውን የሥራ ፕሮግራም ለመተግበር ያላስቻሉትን ሁኔታዎች ማሳየት፤ እና

ለ) የታሰበውን የሥራ ፕሮግራም ማሻሻያ መያዝ አለበት፡፡

3) ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሥራ ፕሮግራም ለውጥ ለማድረግ የቀረበለትን ጥያቄ ከመረመረ በኃላ፡-

ሀ) ተሻሽሎ የቀረበውን የሥራ ፕሮግራም ከተቀበለ ያጸድቀዋል፤ወይም

ለ) ለውጥ ለማድረግ የቀረበውን ጥያቄ ውድቅ ካደረገው ለውሳኔው ምክንያት የሆኑትን ጉዳዮች በመዘርዝር ለአመልካቹ በጹሑፍ ያሳውቀዋል፡፡

## 19) ከፈቃድ ክልል ላይ የተወሰነውን ስለመልቀቅ

1) የምርመራ ፈቃድ እንዲታደስለት የሚጠይቅ ባለፈቃድ በእያንዳንዱ ዕድሳት ወቅት በፈቃዱ ላይ ከተመለከተው የመሬት ክልል ከሩብ እጅ የማያንሰውን ሥፍራ የሚለቅ መሆኑን ማመልከት አለበት፡፡

2) የሚለቀቁ ሥፍራዎች ቅርጽ፤አቀማመጥና ሌሎች ዝርዝር ሁኔታዎች በመመሪያ ይወሰናሉ፡፡

## 20) ይዞ የመቆየት ፈቃድ ስለመስጠት

1) ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሚከተሉት ሁኔታዎች ከተሟሉ ለአመልካቹ የብቸኛ መብት የሚሰጥ ይዞ የመቆየት ፈቃድ ይሰጣል፡-

(ሀ) ባለፈቃዱ በተሰጠው የማዕድን ምርመራ ፈቃድ ክልል ውስጥ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለው የማዕድን ክምችት ማገኘቱን ያሥረዳ ሲሆን፤ እና

(ለ) የተገኘው የማዕድኑ ክምችት ከገበያ ሁኔታ ጋር በተያያዘ ምክንያት ባለ ፈቃዱን የገጠሙት ሌሎች ኢኮኖሚያዊ ጫናዎች ወይም ለማምረት የሚያስፈልገው ቴክኖሎጂ ባለመኖሩ ምክንያት ለጊዜው ማዕድኑን ወደ ማምረት ደረጃ መሸጋገር የማይቻል ሆኖ ከተገኘ፡፡

2) ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በሚከተሉት ሁኔታዎች ይዞ የመቆየት ፈቃድን ሊከለክል ይችላል፡-

(ሀ) ለማምረት የሚያስፈልገው ቴክኖሎጂ መኖሩና የተከማቸውን ማዕድን ውጤታማ በሆነ መንገድ ማምረት እንደሚቻል ግንዛቤ ከተወሰደ፤

(ለ) መልካም የንግድ ፋክክርን መገደብ ከቻለ፤ወይም

(ሐ) የማዕድኑ ሃብት በአመልካቹ እጅ ቁጥጥር ሥር እንዲሰበሰበብ የሚያደርግ ሲሆን፡፡

3) ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ይዞ የመቆየት ፈቃዱን ለአመልካቹ የማይሰጠው ከሆነ ይህንኑ ውሳኔ በጸሑፍ ከነምክንያቱ ለአመልካቹ ያሳውቀዋል፡፡

## 21) ይዞ የመቆየት ፈቃድ ዘመንና ዕድሳት

1) ይዞ የመቆየት ፈቃድ በስምምነቱ ላይ ለተጠቀሰው ጊዜ ተቀባይነት የሚኖረው ሆኖ በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን የዚህ ፈቃድ የቆይታ ዘመን ከ1 (አንድ) ዓመት መብለጥ አይችልም።

2) ይዞ የመቆየት ፈቃድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 20(1) ሥር የተገለጹት መስፈርቶች መኖራቸው ከቀጠለ አንድ አመት ሳልበለጠ ቆይታ ለአንድ ጊዜ ሊታደስ ይችላል።

## 22) ይዞ የመቆየት ባለፈቃድ መብትና ግዴታዎች

1) ይዞ የመቆየት ፈቃድ ያለው ሰው በምርመራ ባገኘው ማዕድን ላይ በፈቃዱ ክልል ውስጥ የማዕድን ማምረት ፈቃድ የማግኘት መብት አለው።

2) ይዞ የመቆየት ባለፈቃድ፦
(ሀ) ያሉትን የገበያና የቴክኒክ ሁኔታዎችና ውጤታቸውን እንዲሁም በተመለከተው ማዕድንና መሬት ላይ ይዞ የመቆየት ፈቃዱ ጸንቶ እንዲቆይ የሚያስፈልግበትን ምክንያት፣ እና
(ለ) የፈቃዱ ዘመን ከመጠናቀቁ በፊት የማዕድን ማምረት ሥራውን ለመጀመር በማድረግ ላይ ያለውን ጥረት፣ የሚያሳይ ዓመታዊ ሪፖርት ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማቅረብ አለበት።

## 23) የከፍተኛና የአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ስለመስጠት

1) ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የከፍተኛና አነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ለጠየቀ ሰው የሚከተሉትን መስፈርቶች ካሟላ ፈቃድ መስጠት ይችላል፦

ሀ) የማዕድን የሥራ ዕቅድ ተቀባይነት ካገኘ፣

ለ) አመልካቹ ከዚህ በፊት በተመሳሳይ ወይም በሌሎች የልማት ዘርፎች ላይ ኢንቨስትመንት ካፒታሉን ሥራ ላያ ያወለ ከሆነና የታቀደውን የማዕድን ልማት ሥራ ለማከናወን የሚያስችለውን የገንዘብ እና የቴክኒክ ብቃት በበቂ ሁኔታ ያለው መሆኑ ከተረጋገጠ፣

ሐ) የፀደቀ የአከባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ካለ፣ እና

መ) አመልካቹ የምርመራ ፈቃድ ወስዶ የነበረ ከሆነና የዚህኑ ግዴታ ያልጣሰ ሆኖ ከተገኘ።

2) የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የማምረት ፈቃድ የማይሰጥ ከሆነ ይህንኑ በጹሁፍ ከነምክንያቱ ለአመልካቹ ያሳውቀዋል።

## 24) የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ዘመንና እድሳት

1) የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ በስምምነት የሚወሰን ሆኖ የቆይታ ጊዜው 5 (አምስት) አመት መብለጥ አይችልም።

2) ባለፍቃዱ ክምችቱን ኢኮኖሚያዊ በሆነ ደረጃ ማምረት መቀጠል የሚችል መሆኑን ካሳየ፣ በፈቃዱ የተመለከቱትን ግዴታዎቹን አሟልቶ ከፈፀመ እና የዚህን አዋጅ ወይም ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ ውስጥ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች አክብሮ ከፈጸመ ፍቃዱን የማሳደስ መብት ይኖረዋል።

3) የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ፈቃድ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በእያንዳንዱ እድሳት ወቅት ከ2 ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ እንዲያገለግል ሊታደስ ይችላል፡፡

## 25) የአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ዘመንና እድሳት

1) የአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ በስምምነት የሚወሰን ሆኖ የቆይታ ጊዜው 3 (ሶስት) አመት መብለጥ አይችልም፡፡

2) ባለፍቃዱ ክምችቱን ኢኮኖሚያዊ በሆነ ደረጃ ማምረት መቀጠል የሚችል መሆኑን ካሳየ፣ በፈቃዱ የተመለከቱትን ግዴታዎቹን አሟልቶ ከፈፀመ እና የዚህን አዋጅ ወይም ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ ውስጥ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች አክብሮ ከፈጸመ ፍቃዱን የማሳደስ መብት ይኖረዋል፡፡

3) የአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ፈቃድ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በእያንዳንዱ እድሳት ወቅት ከ1 ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ እንዲያገለግል ሊታደስ ይችላል፡፡

## 26) የከፍተኛና የአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ባለፈቃዶች መብትና ግዴታዎች

1) የከፍተኛ ወይም የአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ባለፈቃድ ያመረታቸውን ማዕድናት ለገበያ የማስተዋወቅና የመሸጥ መብት ይኖረዋል፡፡
2) የከፍተኛ ወይም የአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ባለፈቃድ፡-
ሀ) ፈቃዱ ተፈጻሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በ6ወራት ውስጥ የምርት ሥራውን መጀመር፤ እና
ለ) የፈቃዱን ስምምነቶችና ግዴታዎች ማክበር አለበት፡፡
ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) ስር የተደነገገው ጊዜ እንደ ፈቃድ ደረጃውና እንደ ማዕድኑ ዓይነት ተመስርቶ በማዕድን ውል ውስጥ ሊራዘም ወይም ሊያጥር ይችላል፡፡

## 27) የሥራ ፕሮግራም ስለመለወጥ

1) የከፍተኛ ወይም የአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ባለፈቃድ ተቀባይነት አግኝቶ የነበረውን የሥራ ፕሮግራም በማናቸውም ጊዜ ለመለወጥ ማመልከት ይችላል፡፡
2) ማንኛውም የሥራ ፕሮግራም ለውጥ ለማድረግ የሚቀርብ ማመልከቻ፡-
ሀ) ተቀባይነት አግኝቶ የነበረውን የሥራ ፕሮግራም ለመተግበር ያላስቻሉትን ሁኔታዎች ማሳየት፤ እና
ለ) የታሰበውን የሥራ ፕሮግራም ማሻሻያ መያዝ፤ አለበት፡፡
3) ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሥራ ፕሮግራም ለውጥ ለማድረግ የቀረበለትን ጥያቄ ከመረመረ በኃላ፡-
ሀ) ተሻሽሎ የቀረበውን የሥራ ፕሮግራም ከተቀበለ ያጸድቀዋል፤ ወይም
ለ) ለውጥ ለማድረግ የቀረበውን ጥያቄ ውድቅ ካደረገው ለውሳኔው ምክንያት የሆኑትን ጉዳዮች በመዘርዘር ለአመልካቹ በጽሁፍ ያሳውቀዋል፡፡

## 28) ልዩ የአነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ስራ ፈቃድ ስለመስጠት

1) ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የሚከተሉት ሁኔታዎች ከተሟሉ የብቻ የሆነ መብት የሚያስገኝ ልዩ አነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ስራ ፈቃድ ለአመልካቹ ይሰጣል፡-
ሀ) የቀረበው የሥራ ዕቅድ ተቀባይነት ካገኘ፤

*ለ) አመልካቹ የታሰበውን የማምረት ስራ ለማከናወን የሚያስችል የገንዘብ አቅም ያለው መሆኑን ካረጋገጠ፤*
*ሐ) የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማው ተቀባይነት ካገኘ፤ እና*
*መ) አመልካቹ ባህላዊ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ የነበረው እና የዚህኑ ግዴታ ያልጣሰ ሆኖ ከተገኘ፡፡*
*ሠ) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(መ) እንደተጠበቀ ሆኖ ለተደራጁ ሥራ ፈላጊ ወጣቶች የባህላዊ ደረጃ ፈቃድ መስጠት ሳያስፈልግ ዘመናዊ የማምረቻ መስሪያ ማግኘት የሚችሉ ከሆነ በኮንስትራክሽንና በኢንዱስትሪ ማዕድናት በቀጥታ የልዩ አነስተኛ ደረጃ የማምረት ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡ የዚህ ዝርዝር አፈጻጸም በሚወጣው ደንብ የሚወሰን ይሆናል፡፡*

## *29) ልዩ የአነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ስራ ፈቃድ ጸንቶ ስለሚቆይበት ጊዜና ዕድሳት*

*1) ልዩ አነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ በፈቃዱ ላይ ለተመለከተው ጊዜ ጸንቶ ይቆያል፤ ሆኖም ይህ ጊዜ ከ2ዓመት በላይ ሊሆን አይችልም፡፡*
*2) ልዩ አነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ በእያንዳንዱ ዕድሳት ወቅት ከ1ዓመት ለማይበልጥ ሶስት ጊዜ ሊታደስ ይችላል፡፡*
*3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) እንደተጠበቀ ሆኖ የልዩ አነስተኛ ደረጃ ባለፈቃድ በፈቃድ ክልሉ ያለው የማዕድን ክምችት በአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ሥራ ፈቃድ ሊያሰራው የሚችል መሆኑ ከተረጋገጠ የፈቃድ ደረጃውን አሻሽሎ ሥራውን መቀጠል ይችላል፡፡*

## *30) ስለባህላዊ ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ*

*1) ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ማመልከቻ ሲቀርብለት አመልካቹ ለፈቃድ ብቁ መሆኑን አረጋግጦ የብቻ የሆነ መብት የሚያስገኝ የባህላዊ ማዕድን ማምረት ፈቃድ ለአመልካቹ ይሰጣል*
*2) የባህላዊ ማዕድን ማምረት ፈቃድ የሚሰጠው በሥራ-ዕድል ፈጠራ ወይም በጥቃቅንና አነስተኛ* ኢንተርፕራይዝ ወይም በሌላ ሕጋዊ አካል ለተደራጁ *ሥራ-ፈላጊዎች* ይሆናል፡፡

*3) የባህላዊ ማዕድን ማምረት ባለፈቃድ፡-*
*ሀ) ለባሕላዊ ማዕድን ማምረት ሥራ በሕግ በተወሰነው የአካባቢ ጥበቃና የጤንነትና የደህንነት ደረጃዎች መሠረት የመስራት ግዴታ አለበት፤*
*ለ) የፈቃዱን ስምምነቶችና ግዴታዎች ማክበር አለበት፡፡*

*4) የባህላዊ የማዕድን ማምረት ፈቃድ በፈቃዱ ላይ ለተገለጸው ዘመን የጸና ይሆናል፤ ሆኖም ይህ ዘመን ከአንድ ዓመት አይበልጥም፡፡*
*5)* የባህላዊ ማዕድን ማምረት *ፈቃድ* ሊታደስ አይችልም፡፡
6) የክምችቱን ኢኮኖሚያዊ አለኝታ በተሻለ ሁኔታ ለማልማት የላቁ የምርመራና የማምረት ዘዴዎችን መጠቀም እንደሚያሥፈልግ ሲታመንበት ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የ45ቀናት የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ በቅድሚያ በመስጠት ባህላዊ የማዕድን ማምረት *ሥራ ፈቃድን* ውል ሊያቋርጥ ይችላል፡፡

## *31) ስለባለፈቃዶች አጠቃላይ መብቶች*

*1) በዚህ አዋጅ ውስጥ እና በሌሎች ህጎች የተደነገጉት ሌሎች መብቶች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ማንኛውም ባለፈቃድ እንደነገሩ አግባብነት የሚከተሉት መብቶች ይኖረዋል፡-*

ሀ) በፈቃዱ ክልል ውስጥ የማዕድን ሥራን ለማከናወን አስፈላጊ የሆኑ ፋብሪካዎችን ማቋቋም፣ ማሺነሪዎች እና እቃዎችን ማስገባት፣ በመሬት ላይ ወይም በመሬት ሥር መሠረተ ልማቶችን የመዘርጋትና የመገንባት፤

ለ) በፈቃዱ ክልል ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ መሠረተ ልማቶችን መዘርጋት፤
ሐ) በፈቃዱ ክልል ውስጥ የሚገኙ የግንባታ ማዕድናትን ከሺያጭ እና ከንግድ አላማዎች ዉጪ መጠቀም፤
መ) ሌሎች ሰዎች እንዲገለገሉበት መሰናክል የማይፈጥር እስከሆነ ድረስ በነባር የመሠረተ ልማት አውታሮች የመገልገል፤እና

ሠ) ፈቃዱ ሌሎች ማዕድናትን እንዲያካትት ወይም የፈቃድ ክልሉ የማዕድን ክምችቱን በሙሉ የማያካትት ከሆነ የማዕድን ክምችቱን ሙሉ እንዲሸፍን ተደርጎ እንዲሻሻልለት የመጠየቅ።
ረ) ከፈቃዱ ክልል ውጭ ለሥራው የሚያሥፈልገውን ሥፍራ በኪራይ እንዲሰጠው የሚመለከተውን አካል የመጠየቅ፤ ሆኖም የኪራይ ውል ግዴታዎቹ በሚመለከተው አካል የሚወሰኑ ሆኖ የሚጸናበትም ዘመን ከማዕድን ሥራ ፈቃዱ ዘመን የእድሳት ጊዜውን ጨምሮ ማለፍ የለበትም።

## 32) የባለፈቃድ አጠቃላይ ግዴታዎች

1) በዚህ አዋጅ ውስጥ እና በሌሎች ህጎች የተደነገጉት ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ማንኛውም ባለፈቃድ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

ሀ) የማዕድን ሥራን በቴክኖሎጂና በማዕድን ኢንዱስትሪ ተቀባይነት ባገኘ የአሰራር ልምድ መሠረት የማካሄድ፤
(ለ) የሰዎችን፤ የወኪሎችን፣ የሠራተኞችንና የሌሎች ደህንነትና ጤንነት የሚያረጋግጥና በተፈጥሮ አከባቢ ላይ ጉዳት ሳያደርስ ወይም የሚደርሰውን ብክለት በሚከላከል ሁኔታ የማዕድን ሥራን የማከናወን፤

(ሐ) በማዕድን ሥራ ላይ ሠራተኞች አስፈላጊ የሆነ ሥልጠናና ትምህርት እንዲያገኙ የማድረግ፤
(መ) በፈቃዱ ክልል፣ በተከራየው መሬትና አዋሳኝ በሆነ መሬት ላይ ሕጋዊ የይዞታ መብት ያላቸውን ሰዎች ላለማወክና ጉዳት ላለማድረስ ተገቢውን ጥንቃቄ የማድረግ፤
(ሠ) ከሌሎች ሰዎች ወይም ከሌሎች ባለፈቃዶች በጋራ ለሚጠቀምባቸው በፈቃዱ ክልል ወይም በተከራየው መሬት ላይ ለተዘረጉ ወይም ለተገነቡ የመሠረተ ልማት አውታሮች በመተባበር ገንዘብ በማዋጣት ማደስና ጥገና ማድረግ፤
ረ) በጤና፣ በደህንነትና አካባቢ ጥበቃን አስመልክቶ የወጡ ህጎችና ድንጋጌዎችን መሰረት አድርጎ የመንቀሳቀስ፤
(ሰ) በማዕድን ማምረት ሥራ ላይ እንቅፋት እስካልሆነ ድረስ በነፃ ወይም ለንግድ ዓላማ ከሆነ ተገቢውን ክፍያ በማስከፈል በተዘረጋው የመሠረተ ልማት አውታሮች ላይ ሌሎች ሰዎች እንዲጠቀሙ የመፍቀድ፤

(ሸ) ተፈላጊውን ችሎታ ላላቸው የሀራችን ዜጎች እና በማዕድኑ አከባቢ ለሚኖሩ ነዋሪዎች ቅድሚያ የሥራ ቅጥር የመስጠት፤

(ቀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 1(ሰ) ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሥራው የሚፈልገው ችሎታ በአገር ውስጥ የሌለ ከሆነ ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ውጪ የውጪ አገር ዜጋን ማሰማራት አይችልም፤

*(በ) በህግ መሠረት የሚፈለግበትን ማንኛውንም ክፍያ በወቅቱ የመክፈል፤ መዛግብቶችና ሪኮርዶችን በባለሥልጣኑ ወይም በሕግ ሥልጣን በተሰጣቸው ሌሎች አካላት እንዲመረመሩ የማቅረብ፤*

*(ተ) የፈቃድ ዘመኑ ሲያበቃ ወይም የፈቃድ ክልሉን ሲለቅ በፈቃድ ክልሉ ላይ የገነባቸውን ግንባታዎች የማስወገድ፤*

*(ቸ) ማንኛውም ባለፈቃድ የማዕድን ማምረት ፈቃድ ወስዶ እየሰራ ባለው ጉዳይ ላይ ከሶስተኛ ወገን ጋር የሚያደርገውን ውል አስመልክቶ በቅድሚያ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡ ከባለሥልጣኑ ዕውቅና ውጭ የሚደረግ ውል ተቀባይነት የለውም፡፡*

*(ኀ) ማንኛውም የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ወስዶ የሚሰራ የሀገር ውስጥ ባለሀብት ፈቃድ በተሰጠው አካባቢ በመንግስት ወይም በማህበረሰቡ በሚካሄዱ የልማት ሥራዎች ላይ በገንዘብም ሆነ በዓይነት ድጋፍ በማድረግ የመሳተፍ ማህበራዊ ግዴታ አለበት፡፡*

*2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሠ እና ረ) መሰረት መሰረተ ልማትን ለመዘርጋትና ለመጠገን የሚያስፈልገው እንዲሁም ለመጠቀም የሚከፈለው የገንዘብ መጠን በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሚወሰን ሆኖ ይሄውም ገንዘብ ከሚሰራው መሠረተ ልማት ጋር የሚመጣጠን መሆን አለበት፡፡*

*3) ባለፈቃዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/1/(በ) መሠረት ያላነሳቸውን ግንባታዎች መንግስት ያለምንም ክፍያ የራሱ ንብረት ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡*

## *33) ስለፈቃድ መደራረብ*

*የዚህ አዋጅ አንቀጽ 35(1) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን በአንድ የፈቃድ ክልል ላይ ለተለያዩ ማዕድናት ፈቃዶች ሊሰጥ ይችላል፡፡ ሆኖም ፈቃድ ሰጭው ባለስልጣን ተደራራቢው ፈቃድ ቀደም ሲል በተሰጠው ፈቃድ መሠረት በሚካሄዱ የማዕድን ሥራዎች ላይ የሚኖረውን ተጽዕኖ መገምገምና ይህንኑ ለቀድሞው ባለፈቃድ ማሳወቅ አለበት፡፡*

## *34) ስለፈቃድ ቀዳሚነት*

*1) ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የማዕድኑን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ወይም ሌሎች አግባብ ያላቸውን የኢንቨስትመንት ዓላማዎችን መሰረት በማድረግ በሌላ አኳኃን ካልወሰነ በቀር፡-*

*(ሀ) የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ፈቃድ በአነስተኛ ደረጃ፤ በልዩ አነስተኛ እና በባህላዊ ደረጃ የማዕድን ፈቃድ እንዲሁም የአነስተኛ ደረጃ ማዕድን ፈቃድ በልዩ አነስተኛና በባህላዊ የማዕድን ፈቃድ ላይ ቀዳሚነት ይኖራቸዋል፡፡*

*ለ) በአንድ የማዕድን ክልል ውስጥ ለተለያዩ የማዕድን ዓይነቶች ከአንድ በላይ የሆኑ ተመሳሳይ ደረጃ ያላቸው ፈቃዶች ከተሰጡ በመጀመሪያ የተሰጠ የማዕድን ሥራ ፈቃድ በሌሎች የማዕድን ሥራ ፈቃዶች ላይ ቀዳሚነት ይኖረዋል፡፡*

*2) ፈቃድ በተሰጠበት ክልል ላይ ለተመሳሳይ ማዕድናት በተደራቢ የተሰጠ ፈቃድ ቢኖር በክርክር ላይ ያለው ክልል በቀዳሚው ባለፈቃድ ይዞታ ሥር እንዳለ ሆኖ ይቆጠራል፡፡*

## *35) ፈቃድ ስለማስተላለፍ*

*1) ይዞ ከመቆየት ፈቃድ ውጪ የማዕድን ሥራ ፈቃድ ያለው ባለፊቃድ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን አስቀድሞ በማሳወቅ ፈቃዱን ለሶስተኛ ወገን ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡*

*2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው ቢኖርም ባለፈቃዱ ወደ ሥራ ሳይገባ ፈቃዱን ሊያስተላልፍ አይችልም።*

*3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው ቢኖርም የባህላዊ የማዕድን ፈቃድ ወይም የልዩ አነስተኛ ደረጃ የማዕድን ሥራ ፈቃድን ለሌላ ሰው ማስተላለፍ አይችልም።*

*4) ማንኛውም ፈቃድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 ሥር የተደነገገውን ፈቃድ የማግኘት መስፈርት ለማያሟላ ሰው ወይም ተቋም ሊተላለፍ አይችልም።*

*5) ማንኛውም ፈቃድ ሲተላለፍ ለዚሁ ጉዳይ በተዘጋጀው መዝገብ ላይ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ካልተመዘገበ በቀር ሕጋዊ ውጤት አይኖረውም።*

6) ፈቃድ ሊተላለፍ የሚችልበት ሁኔታ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ የሚወሰን ይሆናል።

## *36) መብትን ስለመተው*

*1) የአነስተኛ ወይም ከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ባለፈቃድ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በስተቀር ቢያንስ ሶስት (3) ወራት ቀድሞ ማስታወቂያ ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን በጽሁፍ በመስጠት የፈቃድ መብቱን ሊተው ይችላል።*

*2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ድንጋጌ መሰረት መብቱን የተወ ማንኛውም ሰው ውሉ ጸንቶ ለቆየበት ጊዜ የሚያስከትላቸውን ግዴታዎች ከመፈጸም ነጻ አይሆንም።*

## *37) መረጃዎችን ስለመግለጽ*

*1) በዚህ አዋጅ መሰረት በባለፈቃዱ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ወይም ለሌሎች የመንግስት አካላት የሚቀርብ ማንኛውም መረጃ፣ሪፖርት ወይም ሌላ ማስረጃ ፈቃዱ ጸንቶ እስከሚቆይበት ጊዜ ድረስ ከባለፈቃዱ ፍላጎት ውጪ ለሌላ ሰው ሊገለጽ አይችልም።*

*2) መረጃው የሚገለጸው፡-*

*(ሀ) በፍትህ አካላት ለተያዘ ክርክር፣ ማጣራት ወይም ምርመራ ሲሆን፣*

*(ለ) እንደነዚህ ያሉ መረጃዎችን እንዲቀበል በፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ለተፈቀደለት የመንግስት አማካሪ ወይም ሠራተኛ ሲሆን፣ ወይም*
*ሐ) ለጉዳዩ ከሚያሥፈልገው በላይ ዝርዝር እስካልሆነ ድረስ ለመንግስት ወይም መንግስትን በመወከል የማዕድን ሥራዎች ስታቲክስ ለማጠናከር ሲሆን፣በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ክልከላ ተፈጻሚነት አይኖረውም።*

## *38) ስለሪኮርዶችና ሪፖርቶች*

*1) ማንኛውም ባለፈቃድ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችና ማስረጃዎችን በሚከተለው ሁኔታ በማቀናጀት ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡-*

*(ሀ) ከጥልቅ ጉድጓድ ውስጥ ኮር እና የዚህንም ዝርዝር የተመዘገበ ዳታ ጨምሮ፣ የማዕድን ሥራውንና የተገኙ ውጠየቶችን የሚያመለክቱ መረጃዎችን፣*

(ለ) የቅጥር፣የፋይናንስ፣ የንግድ ማስረጃዎችና ሌሎች ህጋዊ የሆኑ መረጃዎች፡፡

2) ባለፈቃዱ ከፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የተሰጠው የጽሑፍ ፈቃድ ሳይኖረው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር በተደነገገው መሰረት ከጥልቅ ጉድጓድ የወጣ ኮር ወይም የኮሩን የተመዘገበ ዳታ ማስወገድ ወይም ማጥፋት አይችልም፡፡

## 39) ስለማዕድናት ባለቤትነት፤ ስለሽያጭና ወደ ውጭ ሀገር ስለመላክ

1) የማዕድን ምርመራ ባለፈቃድ ማዕድን የማውጣት፣ የመመርመርና ይዞ መንቀሳቀስ ይችላል፤አስቀድሞ ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣኑን በማስፈቀድ ናሙናውን ለፍተሻ ወደ ሌላ አካባቢ በመውሰድ ሊያስመረምር ይችላል፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር በተደነገገው መሰረት በባለፈቃዱ ለምርመራ የሚወሰድ ማንኛውም ማዕድን የመንግስት ንብረት ሆኖ ይቀጥላል፤ ከፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ስምምነት ውጭ ባለፈቃዱ ማዕድኑን ሊሸጥ አይችልም፡፡
3) ማዕድን የማምረት ሥራ ባለፈቃድ በፈቃዱ ላይ የተጠቀሱትን ማዕድናት በማውጣት የባለቤትነት መብት ያገኛል፡፡

## 40) የማዕድን መብቶችን ስለማገድና ስለመሰረዝ

1) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/ እና/4/ እንደተጠበቁ ሆነው ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የባለፈቃዱ ተግባር በማህበረሰቡ፤ በአካባቢ ወይም በሠራተኞች ላይ ከባድ አደጋ የሚያሥከትል መሆኑን ሲያምንበትና ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ማገድ ብቸኛው መፍትሔ ሆኖ ሲገኝ ፈቃዱን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ማገድ ይችላል፡፡ ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን እግዱ የሚነሳበትንና ስራ የሚጀምርበትን ቀንም ለባለፈቃዱ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/ እና/4/ ንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ባለፈቃዱ፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ፤ደንብ ወይም በመመሪያ የተጣሉበትን ገንዘብ ነክ ግዴታዎቹን ካልፈጸመ፤
ለ) የማዕድን ሥራዎችን በከባድ ቸልተኝነት ወይም ሆን ብሎ አግባብ ባልሆነ መንገድ ከአካሄደ፤

ሐ) የፈቃዱን መሠረታዊ ስምምነቶች ወይም ግዴታዎች ከጣሰ፤
መ) በሥራ ፕሮግራሙ መሠረት የማዕድን ሥራዎቹን የማያካሂድ ከሆነ፤
ሠ) የጸደቀውን የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማና የጤንነትና ደህንነት ደረጃዎችን ጥሶ ከተገኘ፤
ረ) በዚህ በአዋጅ፤በደንብ ወይም በመመሪያ መሠረት ማቅረብ ከሚገባው ጉዳይ ጋር በተያያዘ ትክክለኛ ያልሆነ ወይም የተሳሳተ መረጃ አቅርቦ ከተገኘ፤
ሰ) የተሟሉ፤ ትክክለኛ የሆኑና ወቅታዊውን ሁኔታ የሚያሳዩ መዝገቦችንና ሪኮርዶችን ካልያዘ፤ ተፈላጊ ሪፖርቶችን ወይም ሌሎች ሰነዶችን በወቅቱ ካላቀረበ ወይም ተፈላጊ ማስታወቂያዎችን በወቅቱ ካልሰጠ፤ ወይም

ሸ) በአግባቡ ስልጣን የተሰጠው የፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ሠራተኛ ወደ ፈቃድ ክልሉ ወይም በኪራይ ወደተያዘው ክልል እንዳይገባ ወይም የማዕድን ሥራዎች የሚካሄዱባቸውን ቦታዎች ወይም ተቋማት ወይም የባለፈቃዱን መዝገቦች፤ ሪኮርዶች ወይም ሌሎች ሰነዶች ወይም ማቴሪያሎች እንዳያይ ካደረገ ወይም በሠራተኛው የተሰጠውን ሕጋዊ ትዕዛዝ ወይም መመሪያ ካልፈጸመ፤

ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ማንኛውንም ፈቃድ ሊሰርዝ ይችላል፡፡

3) ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) መሠረት እርምጃ ከመውሰዱ በፊት የሚከተሉትን የያዘ የጹሁፍ ማስጠንቀቂያ ለባለፈቃዱ ይሰጠዋል፡-

*ሀ) ፈቃዱን ለማገድ ወይም ለመሰረዝ ምክንያት ናቸው የሚላቸውን ነገሮች፤*
*ለ) ባለፈቃዱ የፈጸማቸውን መተላለፎች፤ ጥሰቶች ወይም ጉድለቶች ለማረም ሊወስዳቸው የሚገባቸውን እርምጃዎች፤ እና*
*ሐ) ባለፈቃዱ የፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ሊያይልኝ ይገባል የሚላቸውን ማናቸውም ጉዳዮች በጹሁፍ የሚያቀርብበት ከአምስት የሥራ ቀናት ያላነሰ በቂ ቀን፡፡*

*4) የፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የእገዳ ወይም የስረዛ ማስጠንቀቂያውን የሚያነሳው፡-*

*ሀ) ባለፈቃዱ ለፈቃዱ መታገድ ወይም መሰረዝ ምክንያት ናቸው ተብለው የተዘረዘሩትን ነገሮች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/(ለ) በተሰጠው ማስጠንቀቂያ በተገለጸው ጊዜ ውስጥ በበቂ ሁኔታ ካረመ፤ካሻሻለ፤ ካሰወገደ፤ወይም እንዳይደገሙ ከተከላከለ፤ወይም*
*ለ) እገዳ ወይም ስረዛ ሊፈጸም አይገባም በማለት ባለፈቃዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/3/(ሐ) መሠረት ያቀረባቸውን ምክንያቶች ከተቀበለ፤*

## *<u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>*

## *<u>ስለ ምስክር ወረቀቶች አሰጣጥና አፈጻጸም ሥርዓት</u>*

### *41) ስለምስክር ወረቀት*

*በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት የምስክር ወረቀቶች ሊሰጡ ይችላሉ፡-*
1) *የግኝት ምስክር ወረቀት*
2) *የማዕድን አቅራቢነት ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት*
3) *የማዕድን ዕደ-ጥበብ ብቃት የማረጋገጫ ምስክር ወረቀት*

### *42) ለግኝት የምስክር ወረቀት ስለሚቀርብ ማመልከቻ*

1) የማዕድን መኖር ወይም የማዕድን መኖር ምልክትን ያገኘ ሰው ለዚሁ ጉዳይ በተዘጋጀ ቅጽ ላይ በመሙላት የማዕድን ማግኘት የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በጽሑፍ ማመልከች ሊያቀርብ ይችላል፡፡
2) ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚፈለገው መስፈርት መሟላቱን ካረጋገጠ የማዕድን ግኝት የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው የቀረበውን ማመልከቻ በመቀበል ይመዘግባል፡፡

### *43) የግኝት የምስክር ወረቀት ስለመስጠት*

*ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማዕድን የተገኘበት ሥፍራ ላይ ከዚህ ቀደም ማዕድን እንዳለበት የማይታወቅ፣ ፈቃድ ያልተሰጠ እና ማመልከቻ ያልቀረበበት ወይም የማዕድን ሥራ ያልተከለከለ ከሆነ ማመልከቻው ከደረሰው ቀን ጀምሮ በ15 (አሥራ አምስት) ቀናት ውስጥ ከስትራተጂያዊ ማዕድናት በስተቀር ማዕድኑን ላገኘው አካል የማዕድን ግኝት የምስክር ወረቀት ሊሰጥ ይችላል፡፡*

### *44) የግኝት የምስክር ወረቀት ቆይታና እድሳት*

1) የግኝት የምስክር ወረቀት እስከ 12 (አስራ ሁለት) ወር የሚሰጥ ይሆናል፡፡

2) የግኝት የምስክር ወረቀት አይታደስም፡፡
3) ለግኝት የምስክር ወረቀት የሚሰጥ የመሬት መጠን ቢበዛ ከ5(አምስት) ካሬ ኪሎ ሜትር መብለጥ የለበትም፡፡

## *45) የግኝት የምስክር ወረቀት ባለይዞታ የሆነ ሰው መብትና ግዴታ*

*1)የግኝት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው የግኝቱ ማስረጃ ጸንቶ የሚቆይበት የጊዜ ገደብ ሳይጠናቀቅ በፊት የማዕድን ምርመራ ወይም ማምረት ፈቃድ ማመልከቻ የማቅረብ ወይም ፈቃድ ሰጪውን ባለስልጣን በማስፈቀድ የማግኘት መብቱን ለሌላ ሰው የማስተላለፍ መብት ይኖረዋል፡፡*
*2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የግኝት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ባለፈቃድ ከሆነ የቀድሞው ፈቃዱ ከሱ በፊት የነበሩ ማዕድናትን ወይም ከሱ ፈቃድ ክልል ጋር የሚዋሰነውን ባካተተ መልኩ እንዲሻሻልለት እንደ አማራጭ የመጠየቅ መብት ይኖረዋል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ የተሸሻለው ሥፍራ ሊፈቀድ የሚችለውን ከፍተኛ መጠን መብለጥ የለበትም፡፡*

## *46) የማዕድን የአቅራቢነትና የዕደ-ጥበብ ብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት ብቁ ስለመሆን*

1) ማንኛውም በንግድ ሕግ መሠረት የንግድ ሥራ ማካሄድ የሚችል ሰው በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንብና መመሪያዎች የተገለጹትን ተፈላጊ ሁኔታዎች የሚያሟላ ከሆነ *የማዕድን የአቅራቢነትና የዕደ-ጥበብ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት ይችላል፡፡*

*2) የዚህ አንጽ ንዑስ አንጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም፡-*

*ሀ) በዚህ አዋጅ መሠረት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ሥራውን ከመጀመሩ በፊት አግባብ ካለው የመንግስት መሥሪያ ቤት ተገቢ ሁኔታ በሚሟላት ፈቃድ መውሰድ አለበት፡፡*

*ለ) በዚህ አዋጅ መሰረት የምስክር ወረቀቱ የተሰረዘበት ሰው የምስክር ወረቀት ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ ለሁለት ዓመታት ሌላ የምስክር ወረቀት ማግኘት አይችልም፡፡*

## *47) ስለብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማመልከቻ*

*የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ በጹሁፍ ሆኖ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፡-*

*1) ማመልከቻው ለማዕድን አቅራቢነት ሲሆን፡-*

*ሀ) የአመልካቹ ስም፤የሥራ አድራሻና ዜግነት፤*
*ለ) ሊሰማራበት የፈለገውን የማዕድን ዓይነት፤*
*ሐ) ማዕድኑን ሊገዛበትና ሊሸጥበት ያቀደበት ሥፍራ፤*
*መ) እንደማዕድኑ ዓይነት የሚወሰን ሆኖ ቋሚ የማከማቻ ቦታ እና የመሥሪያ ቦታ ስለመኖሩ ማረጋገጫ፤*
*ሠ) የንግድ ዕቅዱን*
*ረ) በንግድ ሕጉ መሰረት ለንግድ ዕቅዱ ማስፈጸሚያ የሚያስፈልግ ካፒታል መኖሩ ማረጋገጫ፤*

2) ማመልከቻው ለማዕድን ዕደ-ጥበብ ሲሆን፡-

ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ)፣ (ሠ)፣ እና (ረ) የተመለከቱትን
ለ) ኣላስፈላጊ ተረፈ ምርቶችን የሚያስወግድበት ሥርዓት፣
ሐ) በአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ አዋጅ መሠረት የተዘጋጀ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት ሰነድ፣

## 48) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት

1) ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ማመልከቻውን ከተቀበለና አመልካቹ ተገቢ ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላቱን ካረጋገጠ በኃላ ተገቢውን ክፍያ በማስከፈል ለአመልካቹ የምስክር ወረቀቱን ይሰጠዋል፡፡

2) የቀረበው ማመልከቻ ተቀባይነት ካላገኘ ወይም አመልካቹ በሕጉ መሰረት የምስክር ወረቀት ሊሰጠው የማይገባ ከሆነ የምስክር ወረቀቱ አይሰጥም፡፡

3) ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የብቃት ማጋገጫ የምስክር ወረቀቱን የማይሰጥ ከሆነ በ5ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ለአመልካቹ ከነምክንያቱ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 49) ስለብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ዘመን እና እድሳት

1) ማንኛውም የምስክር ወረቀት ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለአንድ ዓመት የጸና ይሆናል፡፡
2) የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው የምስክር ወረቀቱን ለማሳደስ አስፈላጊ የሆኑትን ሁኔታዎች ካሟላና የዚህን አዋጅ ወይም ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የወጡ ደንብ እና መመሪያዎችን በመተላለፍ ለመሰረዝ የሚያበቃ ጥፋት ካልፈጸመ በስተቀር ተገቢውን ክፍያ በመክፈል ለአንድ አመት ጊዜ የማሳደስ መብት ይኖረዋል፡፡

3) ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባለቤት በእያንዳንዱ የምስክር ወረቀት ዘመን ማብቂያ ላይ ማሳደስ አለበት፡፡
4) ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባለቤት ለዕድሳት በሚቀርብበት ወቅት የወቅቱን በጀት ዓመት ግብር ስለመክፈሉ ከግብር ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

## 50) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለማገድና ስለመሰረዝ

1) በዚህ አዋጅ መሰረት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የምስክር ወረቀት ባለቤቱ፡-

ሀ) አግባብነት ባሏቸው ሕጎች መሠረት መያዝ የሚገባውን መዛግብትና ማህደሮች ካልያዘ፣
ለ) ሕጋዊ የግብይት ሰነድ ሳይጠቀም ማዕድናትን ከገዛ ወይም ከሸጠ ወይም ካስተላለፈ፣

ሐ) ተቆጣጣሪዎች ወደ ሥራ ቦታ እንዳይገቡ ከከለከለ ወይም ፈቃደኛ ካልሆነ ወይም መዝገቦች፣ማህደሮች ወይም ሌሎች ሰነዶች እንዳያዩ ካደረገ የምስክር ወረቀቱ ይታገዳል፡፡

2) በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባለቤቱ፡-

ሀ) ሥራውን በራሱ ፈቃድ የተወ እንደሆነ፣
ለ) የምስክር ወረቀቱን ያገኘው የሀሰት መረጃዎችን በማቅረብ ከሆነ፣
ሐ) በዚህ አዋጅ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የምስክር ወረቀቱን ሳያሣድስ ከቀረ፣
መ) በምስክር ወረቀት ላይ ባልተመለከቱ ማዕድናት ግብይት ሥራዎች ላይ ተሰማርቶ ከተገኘ፣

*ሠ) በብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ የተፈቀደለትን ማዕድን ፈቃድ ከሌለው ሰው ከገዛ ወይም ፈቃድ ለሌለው ሰው ከሸጠ ወይም ካስተላለፈ፤*
*ረ) በተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከሚሰራው ሥራ ጋር በተያያዘ ሕገወጥ ግብይት ካካሄደ ወይም የማጭበርበር ተግባር ከፈጸመ፤*
*በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌዎች መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማገድ ምክንያት የሆኑትን ሁኔታዎች በደንብ በሚወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማስተካከል ካልቻለ፤ የምስክር ወረቀቱ ይሰረዛል።*

## *51) ስለብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ክፍያ*

*በዚህ አዋጅ መሠረት የምስክር ወረቀት ለመስጠት፤ ለማሳደስ ወይም ለሌሎች ተያያዥ አገልግሎት የሚጠየቀው ክፍያ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ የሚወሰን ይሆናል።*

## *52) ስለ ክትትልና ቁጥጥር*

*1) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰጪው ባለስልጣን የሚመድባቸው ተቆጣጣሪዎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባለቤት ስራ ቦታ የመግባት፣ናሙና የመውሰድ፣የክትትልና የቁጥጥር ስራዎችን የማከናወን ስልጣን ይኖራቸዋል።*

*2) ተቃጣጣሪዎች ስራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት ሊኖራቸው የሚገቡ ግዴታዎች በደንብ ይወሰናል።*

# *ክፍል አራት*

# *ስለ አስተዳደር*

## *53) የፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ሥልጣንና ተግባር*

***1) በሌሎች ህጎች የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን፦***
*ሀ) የባህላዊ ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ የመስጠት፤*
*ለ) የልዩ አነስተኛ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ የመስጠት፤*
*ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች፦*
*ሐ) የኮንስትራክሽንና የኢንዱስትሪ ማዕድናትን በሚመለከት የምርመራና ይዞ የመቆየት ፈቃዶችን የመስጠት፤*
*መ) የአነስተኛ ደረጃ የኢንዱስትሪ ማዕድናት ማምረት ፈቃዶችን እንዲሁም የአነስተኛና የከፍተኛ ደረጃ የኮንስትራክሽ ማዕድናትን ማምረት ፈቃዶችን የመስጠት፤ ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል።*
*2) ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል*

*ሀ) ለማዕድን ሥራ የሚቀርብ ማመልከቻን ያጸድቃል ወይም ውድቅ ያደርጋል፤*
*ለ) ማንኛውም ባለፈቃድ በፈቃዱ ውስጥ የተገለጹትን ግዴታዎች መወጣቱን፣ የገንዘብ ምንጭና የቴክኒክ ብቃት መኖሩን ያረጋግጣል፤*
*ሐ) በጨረታ በማወዳደር ወይም ቀጥተኛ በሆነ ድርድር መንግስትን ወክሎ የማዕድን ስምምነቶችን የማድረግ፤*
*መ) በዚህ አዋጅ፣ደንብና በመመሪያ መሠረት ፈቃድ የመስጠት፣የማደስ፤ የማገድና የመሰረዝ፤*
*ሠ) የማዕድን ሥራ መረጃዎችና ማስረጃዎችን ይሰበስባል፤ ያቀናጃል፤*
*ረ) የማዕድን ሥራዎች በህጉ መሰረት እየተከናወኑ መሆናቸውን ይቆጣጠራል፣ያረጋግጣል፤*

*ሰ) የባህላዊ ማዕድን ማምረቻ ቦታዎችን በጥናት በመለየት ይከልላል፤*
*ሸ) በዚህ አዋጅና አግባብ ባላቸው በሌሎች ሕጎች መሠረት የሚከፈሉትን ሮያሊቲ፤የመሬት ኪራይና ሌሎች ክፍያዎች የመሰብሰብና ሂሳቡን የመመርመር፤*
*ቀ) የማዕድን ማምረት ሥራ የሚያኪያሄዱ ባለፈቃዶች ተግባራቸው የአካባቢ ጥበቃ ህግን መሰረት ያደረገና ለክልሉ ህዝብ ልማት ድጋፍ የሚያደርግ መሆኑን ያረጋግጣል፤*
*በ) ከማዕድን ማምረት ሥራ የሚሰበሰበውን ገቢ ለህዝቡ ይፋ ያደርጋል፤*
*ተ) የክልሉን ማዕድን ሀብት ማስተዳደር ላይ የማዕድናትን ተፈጥሮና ሥርጭት ለማወቅ የጥናት ሥራዎችን ያካሂዳል ፣ የጂኦሎጂ ካርታዎችን ያዘጋጃል፤መረጃዎችን ያጠናክራል፤ ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፤ የማዕድን ልማት ሥራ እንዲስፋፋ የማስተዋወቅ ሥራ ይሰራል።*

## *54) የማዕድን ሥራዎች ምክር ቤት*

*1) ቢሮውን የሚያማክር የማዕድን ሥራዎች ምክር ቤት ይቋቋማል።*
*2) የማዕድን ሥራዎች ምክር ቤት አባላት ተዋጽዖ፤ኃላፊነትና ሌሎች ዝርዝር ሁኔታዎች በደንብ ይወሰናሉ።*

## *55) ስለ ቁጥጥር*

*1)ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ወይም በየደረጃው ያሉት መዋቅሮቹ የማዕድን ተቆጣጣሪዎችን በመመደብ የማዕድን ልማት ሥራዎችን ሊቆጣጠርና ሊፈትሽ ይችላል።*

*2) የማዕድን ልማት ሥራዎችን እንዲቆጣጠር በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የተመደበ ማንኛውም ተቆጣጣሪ በሥራ ሰዓት ወደ ማዕድን ፈቃድ ክልል ውስጥ በመግባት በሚከተሉት ሥልቶች ቁጥጥርና ፍተሻ ሊያደርግ ይችላል፡-*

*(ሀ) የሚካሄደውን የሥራ እንቅስቃሴ ሁሉ መቆጣጠር፤*

*(ለ) ማንኛውንም መዝገብ፣ ሪከርድ፣ መግለጫ ወይም ሰነዶችን መመርመርና የሰነዱን ቅጂ ክፍል ለምርመራ መውሰድ፤*

*(ሐ) በሥራ ቦታ ያሉትን መሳሪያዎችና አቅርቦት መመርመር፤*

*(መ) ማንኛውም የማዕድን ናሙና መውሰድ፤ መፈተሽ፤ መመርመር፤ መዘርዘርና በየዓይነታቸው መለየት፤ እና*
*(ሠ) በዚህ አንቀጽ መሰረት የቁጥጥር ሥራ ለመስራት የሚያስፈልጉትን የሥራ ድጋፍ ማግኘት።*

*3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን የተመደበ ማንኛውም ተቆጣጣሪ፣ በስራ ሰዓት ወይም በልዩ ሁኔታ ከስራ ሰዓት ውጪ ከፈቃድ ክልል ውጪ ቁጥጥርና ፍተሻ ሊያካሄድ ይችላል።*

*4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) (ለ) መሰረት ማንኛውም መሳሪዎች በመዝገብ መግለጫ ወይም ሰነድ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ቁጥጥር ሥር እንዲቆይ በሚደረግበት ጊዜ፡ (ሀ) በይዞታው ወይም በቁጥጥሩ ሥር የነበረ ሰነድ የተያዘበት ሰው ተቆጣጣሪው እየተከታተለው የሰነዱ ወይም የሰነዱን ክፍል ቅጅዎች እንዲወስድ ማድረግ ይቻላል፣*

ለ) ከተያዙት ንብረቶች፣ መሳሪያዎች፣ መዝገብ፣ መግለጫ ወይም ሰነዶች ጋር በተያያዘ ክስ ካልቀረበበት ወይም በማንኛውም ክርክር ውስጥ ለማስረጃነት ማገልገሉ አጠራጣሪ ሆኖ ሲገኝ ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ለተያዘበት ሰው ወዲያውኑ ይመልስለታል፡፡

5) ተቆጣጣሪው በዚህ አንቀጽ (2) መሠረት ምርመራውን እንዲያካሂድ በፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የተሰጠውን ደብዳቤ አግባብ ላለው የባለፈቃዱ ሠራተኛ የማሳየት ግዴታ አለበት፡፡

# ክፍል አምስት

## ስለ ካሣ ክፍያ፤የአካባቢ ጥበቃና ማሕበረሰብ ልማት

### 56) ስለ ካሣ መርሆዎች

1) ለዚህ አዋጅ አላማ አፈጻጸም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማንኛውንም የማይንቀሳቀስ ንብረት ህጋዊ ለሆነ ባለንብረት አግባብ ባለው ህግ መሰረት የሚወሰን ተመጣጣኝ ካሳ አስቀድሞ እንዲከፈለው በማድረግ ሊወስደው ይችላል፡፡

2) ማንኛውም ባለፈቃድ የማዕድን ሥራ ለማካሄድ መሬት እንዲለቀቅለት የሚጠይቅ ከሆነ ለህዝብ ጥቅም ሲባል የሚለቀቀው የመሬት ይዞታና ለንብረት ካሳ የሚከፈልበት ሁኔታ አግባብነት ባለው ህግ መሰረት የሚወሰን ይሆናል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር የተደነገገው ቢኖርም የመሬት ባለይዞታው ይዞታው ለማዕድን ልማት በባለሀብት የሚወሰድበት ከሆነ በሚካሄደው ልማት ውስጥ ድርሻ እንዲኖረው ይደረጋል፤ አፈጻጸሙ በሚወጣው ደንብ የሚወሰን ይሆናል፡፡

4) ባለሀብቱ ድርሻ እንዲኖረው ፍላጎት ኖሮት ይህን ለማድረግ የሚያስችለው ሁኔታ ከሌለ ባለሀብቱ ለተነሺዎች ከፕሮጀክቱ ተጠቃሚ የሚያደርግ ሌላ ኢኮኖሚያዊ መፍትሄ መፍጠር አለበት፡፡
5) ማንኛውም ባለፈቃድ ከማዕድን ሥራ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ለሚደርሰው ጉዳት ካሳ የመክፈል ሀላፊነት ይኖረዋል፡፡

### 57) ስለ ካሣ ስምምነቶች

1) ማንኛውም ባለፈቃድ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ለባለንብረቱ ስለሚከፈለው ካሣ ከባለንብረቱ ጋር መደራደር አለበት፡፡
2) በባለፈቃዱና ባለንብረቱ መካከል በካሣ ስምምነቱ ሁኔታዎችና ግዴታዎች ላይ ስነምምነት እንደተደረሰ ባለፈቃዱ ወዲያውኑ የስምምነቱን ቅጅ ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ማቅረብ አለበት፡፡

3) ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የተደረገው የካሣ ስምምነት ቅጂ እንደደረሰው ወዲያውኑ ይመዘግበዋል፡፡

4) ስለሚከፈለው ካሣ ስምምነት ላይ መድረስ ያልቻሉ እንደሆነ ባለፈቃዱ ወይም ባለንብረቱ የሚመለከተው የመንግስት አካል እንዲወስንላቸው በጽሁፍ ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡

## *58) ካሣን አስመልክቶ ስለሚቀርብ አቤቱታ ወይም ይግባኝ*

*1) ካሣን አስመልክቶ የሚቀርብ አቤቱታ ወይም ይግባኝ የመሬት ይዞታን ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ለማስለቀቅና ለንብረት ካሳ ስለሚከፈልበት ሁኔታ ለመወሰን በወጣ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ይፈጸማል፡፡*
*2) ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ከማዕድን ሥራ ጋር በተያያዘ መሬትን ካሳ በመክፈል ማስለቀቅ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ መሬትን ለሕዝብ ጥቅም ካሳ ተከፍሎ እንዲለቀቅ የማድረግ ሥልጣን ከተሰጠው መሥሪያ ቤት ጋር በመመካከር ሥራውን በአፋጣኝ የሚፈጸምበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡*

## *59) የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማና የመልሶ ማቋቋሚያ ፈንድ*

*1) በባህላዊ ዘዴ ማዕድን ማምረትና ይዞ መቆየት ፈቃድ ከሚጠይቅ ሰው በስተቀር፣ የማዕድን ፈቃድ እንዲሰጠው የሚጠይቅ ማንኛውም አመልካች ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ የአካባቢና ህብረተሰብ ተጽዕኖ ዳሰሳ ጥናት ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡*

*2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የባህላዊ ዘዴ ማዕድን ማምረት ባለፈቃድ የተቆፈረውን ጉድጓድ መልሶ መድፈንና የተቆረጠውን እንጨት መተካት አለበት፡፡*

*3) በባህላዊ ዘዴ ማዕድን ማምረትና ይዞ መቆየት ፈቃድ ካለው ሰው በስተቀር፣ ማንኛውም ባለፈቃድ በአካባቢና ህብረተሰብ ላይ የሚደርሰውን ተጽዕኖ መልሶ ለማልማት የሚያስፈልገውን አጠቃላይ ፈንድ መመደብ አለበት፡፡*

*4) ባለፈቃዱ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በሚያዘው መሰረት ለመልሶ ማልማት የሚወሰነውን የፈንድ ገንዘብ በሚከፈተው ዝግ የባንክ ሂሳብ ቁጥር በየአመቱ በአመቱ የመጀመሪያ ወር ላይ ማስገባት አለበት፡፡*

*5) በሚመለከተው አካል በጸደቀው የአካባቢና ህብረተሰብ ተጽዕኖ ግምገማ ሰነድ ላይ የሚቀመጠው ፈንድ ለመልሶ ማልማት የሚያስፈልገውን አጠቃላይ ወጪ የሚሸፍን ስለመሆኑ በአጽዳቂው አካል በሚገባ መታየት አለበት፡፡*

*6) ማንኛውም የማዕድን ማምረት ባለፈቃድ በህጋዊ ሁኔታ በፈቃድ ክልሉና በስምምነት በሚወሰነው መሰረት በዚያ አካባቢ የሚኖሩትን ህብረተሰብ በማህበራዊ ልማት ዕቅድ ላይ በማሳተፍ ለዚህ ልማት የሚያስፈልገውን ፈንድ መመደብ አለበት፡፡*
*7) የዚህ አንቀጽ ዝርዝር አፈጻጸም በሚወጣው ደንብ የሚወሰን ይሆናል፡*

# *ክፍል ስድስት*

# *ከማዕድን ሥራዎች ስለሚሰበሰብ ሮያሊቲ፤የገቢ ግብርና ሌሎች ክፍያዎችና ገንዘብ ነክ ጉዳዮች*

## *60) ሮያሊቲ*

*1) የማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ የተመረተውን ማዕድን በንግድ ልውውጥ ውስጥ ከሸጠበት ዋጋ ላይ ሮያሊቲ ይከፍላል፡፡*
*2) የሮያሊቲ መጠንና የአከፋፈል ሁኔታ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ የሚወሰን ይሆናል፡፡*

## 61) ለጊዜው ስለሚተመን የሮያሊቲ መጠን

1) መከፈል የሚገባውን የሮያሊቲ መጠን ለመተመን በማይቻልበት ጊዜ ባለፈቃዱ ጊዜያዊ የሮያሊቲ ክፍያ ይከፍላል።
2) መከፈል ያለበት ሮያሊቲ መጠን ሲረጋገጥ ባለፈቃዱ ልዩነቱን ይከፍላል።
3) ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ማንኛውም ባለፈቃድ የሚጠይቀውን የሮያሊቲ ክፍያ ለመቀነስ፣ለጊዜው ለማንሳት ወይም ለማስቀረት አግባብ ላለው የመንግስት አካል ሃሳብ በማቅረብ ሊያስወስን ይችላል።

## 62) የገቢ ግብር

የከፍተኛ፣ አነስተኛና ልዩ አነስተኛ የማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት የገቢ ግብር አዋጅ መሰረት ከማዕድን ሥራ ከሚያገኘው ገቢ ለክልሉ መንግስት የገቢ ግብር ይከፍላል። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

## 63) መረጃ ስለመሰብሰብ

1) ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ማንኛውም ባለፈቃድ ከሮያሊቲው ክፍያ ጋር በተያያዘ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ማክበሩን ለማረጋገጥ ማናቸውንም የቃል፣የጽሁፍ ወይም የኤሌክትሮኒክስ መረጃ እንዲያቀርብ ወይም እንዲያሳይ በጽሁፍ ማዘዝ ይችላል።
2) ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚያስፈልጉ መረጃዎች እንዳይቀርቡ ወይም እንዲጠፉ ተደርገዋል ብሎ ሲያምን በዚህ አዋጅ አንቀጽ (56) መሠረት ምርመራ እንዲካሄድ ሊያዝ ይችላል።

## 64) ሮያሊቲና የገቢ ግብር ስላለመክፈል

ባለፈቃዱ መከፈል ባለበት ጊዜ ውስጥ ሮያሊቲ፣የገቢ ግብር ወይም ማናቸውንም ሌላ ክፍያ ሳይከፍል ከቀረ፣ ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ያልተከፈሉ ክፍያዎች ተጠናቀው እስኪከፈሉ ወይም ክፍያውን ለመፈጸም የሚያስችል በፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ተቀባይነት ያለው ዘዴ እስኪመቻች ድረስ ጉዳዩ ከሚመለከተው ማንኛውም የማዕድን ማምረቻ ቦታ ምንም ዓይነት ማዕድን እንዳይነሳና እንዳይሸጥ በመከልከል ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

## 65) የመሬት ኪራይ

1) ማንኛውም ባለፈቃድ በፈቃዱ ላይ ለተመለከተው ክልል የመሬት ኪራይ በየዓመቱ በቅድሚያ ይከፍላል። የኪራዩ መጠን እንደፈቃዱ ዓይነትና ደረጃ በክልሉ በሚወጣው የገቢዎች ደንብ የሚወሰን ሆኖ ማናቸውም የኪራዩን መጠን የሚለውጥ የሕግ ማሻሻያ ተፈጻሚ የሚሆነው ማሻሻያው ከወጣበት ቀን በኃላ በሚሰጡ ፈቃዶች ላይ ብቻ ይሆናል።

2) ማንኛውም ባለፈቃድ ከፈቃድ ክልል ውጭ በኪራይ ለያዘው መሬት በየዓመቱ በቅድሚያ ኪራይ ይከፍላል። የኪራዩ መጠን የኪራዩ መብት በተመሠረተበት ሰነድ የሚወሰን ሆኖ በሰነዱ ውስጥ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በስተቀር እስከ ኪራዩ ዘመን መጨረሻ የጸና ይሆናል።

## 66) ስለ ፈቃድ ክፍያ

በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚሰጡ ፈቃዶችና የምስክር ወረቀቶች እንዲሁም ፈቃዶችን ወይም የምስክር ወረቀቶችን ለማሳደስ ክፍያ ይከፈላል፡፡ የክፍያው መጠንና የአከፋፈሉ ሁኔታ በደንብ ይወሰናል፡፡

## 67) በመንግስት ስለሚያዝ አክሲዮን

መንግስት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 መሠረት የማዕድን ሥራዎች የማካሄድ መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በማንኛውም ባለፈቃድ ከሚካሄድ የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራዎች ኢንቨስትመንት እስከ አምስት በመቶ የሚደርስ አክሲዮን ያለምንም ክፍያ ሊይዝ ይችላል፡፡ እንዲሁም ስለድርሻው በመቶኛ፣ስለአከፋፈሉ፣ከተሳትፎ ስለሚመነጭ መብትና ግዴታዎቹ እና ሌሎች የተሳትፎ ዝርዝር ሁኔታዎች በስምምነት በሚወሰነው መሠረት መንግስት ተጨማሪ አክሲዮኖችን ሊይዝ ይችላል፡፡

## 68) ከጉምሩክ ቀረጥና ከታክስ ነጻ በተመለከተ

ለማዕድንሥራዎች የሚያሥፈልጉ መሣሪያዎችን፣ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነጻ ስለማስገባት የተደነገጉ ሌሎች ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው ባለፈቃዱ፡-

1) የማዕድን ልማት ሥራዎች ለመፈጸም በቅድሚያ ለሥራው የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች፣ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎች ለማዕድን ማምረት ሥራ አስፈላጊ መሆናቸውን በፕሮጀክቱ አዋጪነት ጥናት ውስጥ የተመለከቱ መሳሪያዎችን ብቻ ከቀረጥ ነጻ እንዲገቡለት ከፈለገ ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣኑን የድጋፍ ደብዳቤ ሊሰጠው ይችላል፡፡

2) ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡት መሣሪያዎች፣ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎች ለማዕድን ሥራ ብቻ መዋላቸውን ይከታተላል፤ ለታለመለት ዓላማ አለመዋላቸውን ካረጋገጠ ግን ለሚመለከተው አካል ያሣውቃል፡፡

## 69) ስለባለፈቃዶች ምዝገባ

1) ማንኛውም ባለፈቃድ አግባብ ባለው ባለሥልጣን ዘንድ በንግድ መዝገብ ላይ የመመዝገብና ለፈቃዱ ዘመን በክልሉ ውስጥ ጽሕፈት ቤት የማቋቋም ግዴታ አለበት፡፡
2) ባለፈቃዱ በፈቃዱ ላይ የተመለከቱትን ማዕድናት ለማምረት፣ለመሸጥ ወይም ወደውጭ አገር ለመላክ ወይም ለሥራዎቹ አስፈላጊ የሆኑ ዕቃዎችን ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት ወይም የአዕምሮ ሥራዎችን በውል ለማግኘት ከሌላ የመንግስት መሥሪያ ቤት ፈቃድ አያሥፈልገውም፡፡

3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ የባለፈቃዱን የጉምሩክና የባንክ ፎርማሊቲዎች የሚሟላት ግዴታ አያስቀርም

## 70) ስለመንግስት ድጋፍ

1) መንግስት፡-

ሀ) የክልሉን ወቅታዊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመፍታት እገዛ ለሚያደርጉ የማዕድን ሥራዎች፣

ለ) ማዕድናትን በማበልጸግ በክልሉ ውስጥ ተጠቃሚነትን ለሚያሥፋፉ የማዕድን ሥራዎች እና

ሐ) በማህበር ተደራጅተው ለሚንቀሳቀሱ የባህላዊ የማዕድን ሥራዎች፣ ማበረታቻና ድጋፍ ሊያደርግ ይችላል፡፡

2) የማበረታቻውና የድጋፉ ዓይነትና ሁኔታ የማዕድን ሥራውን መሠረት ያደረገ ሆኖ በደንብ ይወሰናል፡፡

# ክፍል ሰባት

# ስለ ቅሬታ አቀራረብና ስለ አለመግባባቶች አፈታትና አስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት

## 71) አለመግባባቶችን ስለመፍታት

1) የማዕድን ምርመራ፣ ይዞ መቆየት ወይም ማምረትን ከተመለከተ ስምምነት በመነጨ፣ በስምምነቱ አተረጓጎም፣መጣስ ወይም መቋረጥ ምክንያት ወይም ከእነዚሁ ጋር በተያያዙ ምክንያቶች በመንግስትና በባለፈቃድ መካከል የሚፈጠር ማንኛውም ክርክር፣አለመግባባት ወይም የይገባኛል ጥያቄ በተቻለ መጠን በጋራ ውይይት ይፈታል፡፡

2) ጉዳዩ በጋራ ውይይት ሊፈታ ካልቻለ በስምምነቱ ውስጥ በተመለከተው ሥነ ሥርዓት መሠረት በግልግል ዳኝነት ታይቶ ይወሰናል፡፡ በግልግል ዳኝነተት የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻና በተዋዋይ ወገኖች ላይ የጸና ይሆናል፡፡

3) በግልግል ዳኝነት በሚሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ወገን ቅሬታውን ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ይግባኝ እንዲታይለት ማቅረብ ይችላል፡፡

## 72) ስለ ፈቃድ መብት መቋረጥ

1) የፈቃድ መብት፡-

ሀ) ባለፈቃዱ የፈቃዱን ክልል በሙሉ ሲለቅ ወይም የፈቃድ መብቱን ሲተው፣
ለ) በዚህ አዋጅ፣ደንብና መመሪያ መሠረት ፈቃዱ በፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ሲሰረዝ፣
ሐ) የፈቃዱ ዘመን ከተፈጸመ በኃላ ሳይታደስ ሲቀር፣ወይም
መ) የወራሾች መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ባለፈቃዱ ሲሞት ወይም ባለፈቃዱ የንግድ ድርጅት ከሆነ ሲፈርስ ወይም የመክሰር ውሳኔ ሲሰጥበት፣
ይቋረጣል፡፡

2) በስምምነት በሌላ ሁኔታ ካልተገለጸ በቀር የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ሲቋረጥ ለማዕድን ሥራዎች ጥቅም ላይ ውለው የእርጅና ቅናሻቸው ሙሉ በሙሉ ያልተፈጸመውን የማይንቀሳቀሱና ተንቀሳቃሽ ንብረቶች በባለፈቃዱ የሂሳብ መዝገብ ላይ በሚታየው ዋጋቸው መንግስት ሊወስዳቸው ይችላል፡፡ መንግስት በዚህ መብቱ ካልተጠቀመ ባለፈቃዱ አግባብ ባላቸው ሕጎች መሠረት ንብረቶቹን ለሌላ ሰው ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡ ይህ የማይሆን ከሆነ ስለ አካባቢው ጥበቃ በገባቸው ግዴታዎች መሠረት እንዲያስወግዳቸው ይገደዳል፡፡

## 73) ስለ አስተዳደራዊ እርምጃዎችና ቅጣት

1) ሮያልቲን፣ የገቢ ግብርንና ሌሎች ገንዘብ ነክ ጉዳዩችን በተመለከተ ስለሚወሰዱ አስተዳደራዊ እርምጃዎች በሚወጣው ደንብ የሚወሰን ይሆናል፡፡

2) የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የተላለፈ ወይም በማናቸውም ሁኔታ አፈፃፀማቸውን ያሰናከለ ማንኛውም ሰው አግባብ ባላቸው የኢትዩጲያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ ድንጋጌዎች መሠረት ይቀጣል፡፡

## 74) ስለቅሬታ አቀራረብ

1) በዚህ አዋጅ መሰረት በተሰጠ አስተዳደራዊ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ቅሬታውን በየደረጃው ለሚገኙ የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ኃላፊዎች ማቅረብ ይችላል፡፡

2) ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በተሰጠ አስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ ይግባኝ እንዲታይለት ለፍርድ ቤት ማቅረብ የሚችለው በፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ያሉ አስተዳደራዊ መፍትሔዎች በሙሉ ተሟጠው ካለቁ በኃላ ነው፡፡

# ክፍል ስምንት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 75) የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

1) ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተሰጠ ፈቃድ ወይም የተደረገ የማዕድን ስምምነት ከዚህ አዋጅ ጋር እስካልተቃረነ ድረስ ጸንቶ ለሚቆይበት ቀሪ ዘመን ተፈጻሚነቱ ይቀጥላል፡፡ ከዚያም በዚህ አዋጅ ድንጋጌች መሠረት ሊታደስ ይችላል፡፡

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ ቢኖርም አንደኛው ወገን አግባብ ባለው ስምምነት ከሚያካሂደው የማዕድን ስራ በሚገኘው ጥቅም ላይ በዚህ አዋጅ ምክንያት ጉዳት የደረሰ እንደሆነ ጉዳት የደረሰበት ወገን ሲጠይቅ ሁለቱም ወገኖች በቅን ልቦና ተወያይተው አስፈላጊውን ማስተካከያ ለማድረግ ሊስማሙ ይችላሉ፡፡

3) ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተፈጠረ ለክስ መነሻ የሚሆን ጉዳይ ወይም የተጀመረ የክርክር ወይም የአፈጻጸም ሂደት ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ጸንተው በነበሩ ሕጎች መሠረት ፍጻሜ ያገኛል፡፡

## 76) ቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት

ከማዕድን ሥራዎች ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸውን የንግድ፣ የገቢ፣ የስራ ዕድል ፈጠራ፣ ኢንቨስትመንት፣ የአካባቢ ጥበቃ እና ሌሎች ጉዳዮችን አስመልክቶ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ተፈጻሚ ለማድረግ በሚደረገው እንቅስቃሴ የሚመለከታቸው ተቋማት

*ተቀናጅተው የሚሰሩበት ቅንጅታዊ የአሰራር ሥርዓት እንዲኖር ይደረጋል። የዚህ አንቀጽ ዝርዝር በሚወጣው ደንብ የሚወሰን ይሆናል።*

## *77) የመተባበር ግዴታ*

*ማንኛውም ሰው ለዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ተግባራዊነት የመተባበር ግዴታ አለበት።*

## *78) ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች*

*የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፤ደንብ፤ መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተሸፈኑትን ጉዳዮች በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም።*

## *79) ደንብና መመሪያ ስለማውጣት*

*1) የክልሉ መንግስት አስተዳደር ምክር ቤት ይህንን አዋጅ በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።*

*2) ቢሮው ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የወጡ ደንቦችን በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።*

*3) ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ይህ አዋጅ፤ደንቦችና መመሪያዎች በትክክል በሥራ ላይ መዋላቸውን የመከታተልና የመቆጣጠር ሥልጣን ተሰጥቶታል።*

## *80) አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ*

*ይህ አዋጅ በክልሉ ምክር ቤት ከፀደቀበት የካቲት------ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።*

**አርባ ምንጭ**

**የካቲት - ቀን 2016 ዓ.ም**

**ጥላሁን ከበደ**

**የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር**